## በተፈጥሮ ፡ መወለድ ፡ በኩል ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አስተዳደግ ፤

ክፎ ፡ ክሸችኖቢች ፡

የሕግ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ።

### ሀ. መግቢያ ፤

፩ / ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ በመኖር ፡ ስለሚወለዱ ፡ ልጆች ።

በሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ «ኃጢአት ፡» የሚለው ፡ ሐሳብ ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ በሚወለድና ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ በሚወለድ ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ እንዲፈጠር ፡ አድርጎአል ። ይህም ፡ በውርስ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ በሁለቱ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አስከትሏል ። በ፲፯ኛው ፡ ክፍለ ፡ ዘመን ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ በጥንታዊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ መሠረት ፡ ኑዛዜ ፡ ካልተደረገላቸው ፡ በስተቀር ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት መኖር ፡ የተወለዱ ፡ ልጆች ፡ ሊወርሱ ፡ አይችሉም[1] ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ይህም ፡ ልዩነት ፡ ዘለቄታ ፡ አላገኘም ፤ ወይም ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አልዋለም ፡ ነበር ። ልማዳዊ ፡ ሕግም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ በሚወለድና ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ በሚወለድ ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አላደገረም ።[2]

፪ / ስለ ፡ መወለድ ፤

ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ስለማንኛውም ፡ የተወላጅነት ፡ ማስረጃ ፡ ዓይነቶች ፡ እንዳችም ፡ ድንጋጌ ፡ አልነበረውም ። (በነገራችን ፡ ላይ ፡ የዚህ ፡ ድንጋጌ ፡ አለመኖር ፤ ከላይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ የተጠቀሰው ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ በሚወለድና ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ በሚወለድ ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ ጥንታዊ ፡ ልዩነት ፡ በርግጥ ፡ ይኑር ፡ አይኑር ፡ አጠራጣሪ ፡ አድርጎታል ፡) በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. ከወጣው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ በፊት ፡ በነበረው ፡ ልማዳዊ ፡ ሕግ ፡ መሠረት ፡ ማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ የተወላጅነት ፡ ማስረጃ ፡ የተፈቀደ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የልጅነት ፡ ማስረጃ ፡ የተወሰነ ፡ መንገድ ፡ አልነበረውም ። አባትነትን ፡ ለማሳወቅ ፡ አንዱ ፡ በጣም ፡ የተለመደ ፡ የማስረጃ ፡ መንገድ ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ እናት ፡ አባት ፡ ነው ፡ የተባለውን ፡ ሰው ፡ (አግብታም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይህ ፡ አባት ፡ ነህ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ከባሏ ፡ ሌላ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ፡) በማመልከት ፡ «አባት ፡ ነው ፡» ብላ ፡ የምትሰጠው ፡ ቃለ ፡ መሃላ ፡ ነበረ ። እንዲህ ፡ ዐይነቱን ፡ መሃላ ፡ እንዲት ፡ ያላገባች ፡ ሴት ፡ የፈጸመች ፡ እንደሆነ ፡ የተለየ ፡ ጽናት ፡ ይኖረዋል ። መሐላውም ፡ ከቁስ ፡

1. ጉይዲ ፡ ኢል ፡ ፍትሐ ፡ ነገሥት ፡ ኦ ፡ ሊጀስላሲዮን ፡ ዴይ ፡ሬ ፡ (ሮማ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ፲፰፻፺፱ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ ገጽ ፡ ፪፻፲፱ ፡ እና ፡ ፭፻፺፪ ።
2. ለምሳሌ ፡ ሲ ፡ ኮንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ ፕሪንቺፒ ፡ ዲ ፡ ዲሪቶ ፡ ኮንሱኤ ፡ ቱ ፡ ዲናሪዎ ፡ ዴል ፡ ኤሪትሪያ ፡ (ሮማ ፡ ፲፱፻፲፮) ፡ ገጽ ፡ ፫፻፲፭ ፤ ኤፍ ፡ ኦስቲኒ ፡ ትሬታቶ ፡ ዴል ፡ ዲሪት ፡ ኮንሱኤ ፡ ቱዲና ኤርትሪያ ፡ (አስመራ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ፲፱፻፶፮) ፡ ገጽ ፡ ፹ ፡ አስተያይ ።

ፊት ፡ ልጅ ፡ በሚጠመቅበት ፡ ጊዜ ፡ ወይም ፡ ቤቲቱ ፡ ልትሞት ፡ ስታጣጥር ፡ እንደ ፡ መጨረሻ ፡ ቃሏ ፡ ከተሰጠ ፡ በመከላከያ ፡ ማስረጃ ፡ ለማፍረስ ፡ በጣም ፡ ከባድ ፡ ነበር ።[3]

እንግዲህ ፡ ሀ) ልጅነት ፡ እንዲህ ፡ በቀላሉ ፡ ሊረጋገጥ ፡ መቻሉ ፤ ለ) ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ በተወለደና ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ በተወለደ ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ ልዩነት ፡ አለመኖሩና ፡ የሁለቱ ፡ መብት ፡ መስተካከሉ ፤ ሐ) ተወላጅነትን ፡ ለማሳወቅ ፡ ክስ ፡ የሚቀርብበት ፡ ጊዜና ፡ ተወላጅነት ፡ የሚያስከትለው ፡ የውርስ ፡ ክስ ፡ የሚቀርበት ፡ ጊዜ ፡ አለመገደቡ ፡ በቂ ፡ ምክንያቶች ፡ ሳይኖራቸው ፡ በጥቃቅን ፡ ምክንያቶች ፡ እየተነሱ ፡ ልጅ ፡ ነን ፡ በሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ለሚቀርቡ ፡ እጅግ ፡ የበዙ ፡ የውርስ ፡ ክሶች ፡ ምክንያት ፡ ሆኖ ፡ ነበር ።[4] ይህን ፡ የተዘበራረቀ ፡ ሁኔታ ፡ ለመቋቋም ፡ በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. የወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ፡ብሔር ፡ ሕግ ፡ በሀገሩ ፡ ባህል ፡ የተለመደውን ፡ በሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ የተወለደውን ፡ ልጅና ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ የተወለደውን ፡ ልጅ ፡ መብት ፡ እኩል ፡ እንዲሆን ፡ አድርጎአል ። ነገር ፡ ግን ፡ ልጅነትን ፡ ለማሳወቅ ፡ ማቅረብ ፡ የሚቻሉትን ፡ የማስረጃ ፡ ዐይነቶች ፡ በጣም ፡ <u>ወስኗል</u> ። እነዚህን ፡ የማስረጃ ፡ ዐይነቶች ፡ ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ እንመረምራለን ።

### ለ. የልጅነት ፡ ማስረጃ ፡ ዐይነቶች ፡[5]

#### <u>አጭር ፡ መግለጫ ፤</u>

የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የምዕራፍ ፡ ፲ ፡ መክፈቻ ፡ ቁጥር ፡ እንደሚለው ፤ ሕጉ ፡ በግልጽ ፡ ስምምነቶችን ፡ ካልፈቀዳቸው ፡ በቀር ፡ አባትንና ፡ እናትን ፡ ስለ ማወቅ ፡ የተሰጡት ፡ በስምምነት ፡ ሊለወጡ ፡ አይቻልም ።[6] ይህ ፡ ከሆነ ፡ እንግዲህ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የአባትንና ፡ የእናትን ፡ ማወቂያ ፡ ዓይነቶች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ (በተጠቀሰው ፡ ምዕራፍ ፡ በክፍል ፡ ፩ ፡ ውስጥ ፡) መዘርዘሩ ፡ እነዚህ ፡ የማወቂያ ፡ ዐይነቶች ፡ ገደብ ፡ የሚያበጁ ፡ መሆናቸውን ፡ ለመግለጽ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ገደብ ፡ ለክፍል ፡ ፪ ፡ በውል ፡ ለሚወሰነው ፡ አባትነት ፡ አያገለግልም ። አባትነትን ፡ ወይም ፡ እናትነትን ፡ የሚያሳውቁ ፡ ዘዴዎች ፡ አባትነት ፡ ወይም ፡ እናትነት፡ መታወቁን ፡ <u>ከሚያረጋግጡ</u> ፡ ዘዴዎች ፡ መለየት ፡ አለባቸው ። አባትነት ፡ ወይም ፡ እናትነት ፡ መረጋገጡን ፡ የሚያሳዩ ፡ ዘዴዎች ፡ በምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ ውስጥ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ትእዛዛዊ ፡ ቍጥሮች ፡ ተወስነዋል ።

---

3. ለምሳሌ ፡ ከላይ ፡ በሁለተኛው ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ የግርጌ ፡ ማስታወሻ ፡ ስር ፡ የተመለከተውን ፡ የቢክንቲ ፡ ሮሲኒ ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፪፻፺፮—፪፻፺፯ ፤ ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የአስቲኒን ፡ መጽሐፍ ፡ ገጽ ፡ ፰ ፡ አስተያይ ።
4. አብዛኛውን ፡ ያልገለጸው ፡ የልምድ ፡ ሕግ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ እንደሚያመለክተው ፡ በከባድ ፡ ምክንያት ፡ ላይ ፡ ለተመሠረተ ፡ ጉዳይ ፡ (በግልጽ ፡ ያልሆነ ፡ የልጅነት ፡ ማወቅ ፡ ትራክታተስ) ፡ የእነ ፡ ሙሉነሽ ፡ ኃይሉና ፡ የበቀለች ፡ ኃይሉን ፡ ጉዳይ ፡ ጠቅላይ ፡ ን ፡ ነ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ይግባኝ ፡ መዝገብ ፡ ቍጥር ፡ ፴፯/፶፯ ፡ ተመልከት ። (ያልታተመ)
5. የወርቅነሽ ፡ በዛብህንና ፡ የይድነቀውን ፡ ጉዳይ ፡ አስተያይ ፡ (ጠቅላይ ፡ ን ፡ ነ ፡ ፍ/ቤት ፡ ፲፱፻፶፩) ፡ <u>የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፩ኛ ፡ ቮልዩም</u> ፡ ገጽ ፡ ፲፯ ።
6. በእንግሊዝኛው ፡ ፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ያላግባብ ፡ "አስርቴንሜንት" ፡ ተብሎ ፡ ተተርጉሟል ።

በሕግ ፡ ውስጥ ፡ በአንዲት ፡ ሴት ፡ ወይም ፡ ባንድ ፡ ሰውና ፡ ባንድ ፡ ልጅ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ የመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሥጋ ፡ ዝምድና ፡ መኖሩን ፡ የሚያሳዩ ትን ፡ የማስረጃ ፡ ዓይነቶች ፡ (በቤተ ፡ ሰብ ፡ ሕግና ፡ በውርስ ፡ ሕግ ፡ ከሚያስከት ለው ፡ ውጤት ፡ ጋር ፡) ከታች ፡ እንደተለመከተው ፡ ባጭሩ ፡ መግለጥ ፡ ይቻላል ።

፩ / እናትነት ፡ የአንድ ፡ ልጅ ፡ ካንዲት ፡ ሴት ፡ መወለድ ፡ በቀላሉ ፡ ለእናት ነት ፡ ማስረጃ ፡ ይሆናል [7] ።

፪ / እናትነትን ፡ እንዲህ ፡ በቀላሉ ፡ ማሳወቅ ፡ ከተቻለ ፡ አባትነትም ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ በመፀነሱ ፡ መረጋገጥ ፡ ይገባው ፡ ነበር ። ግን ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ መፀነሱን ፡ መወሰን ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሕጉ ፡ ከሚከተ ሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ወይም ፡ ተግባሮች ፡ ጋር ፡ አባትነትን ፡ ያያይዛል ። እነዚህ ፡ ሁኔታዎች ፡ ወይም ፡ ተግባሮች ፡ ከእውነተኛው ፡ ከግብረ ፡ ሥጋ ፡ እርግዝና ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ሊሆኑ ፡ ይችላሉ [7] ።

፫ / አንድ ፡ ልጅ ፡ በተወለደበት ፡ ወይም ፡ በተፀነሰበት ፡ ጊዜ ፡ በወላጂቱ ፡ እናትነትና ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ መካከል ፡ ጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የኖረ ፡ እንደሆነ ፡ ከሴቲቱ ፡ እናትነት ፡ (ይህ ፡ በልጁ ፡ መወለድ ፡ ይታወቃል ፡) የሰውየውን ፡ አባትነት ፡ ለማስረዳት ፡ ይቻላል [8] ። ይህም ፡ ማለት ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ ከእናቲቱ ፡ ጋር ፡ የጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ነው ።

፬ / ከላይ ፡ በ (ሀ) ተራ ፡ ቁጥር ፡ አባትነትን ፡ ማስረዳት ፡ ካልተቻለ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አንድን ፡ ልጅ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ በማለቱ ፡ አባትነቱን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ይችላል [9] ።

፭ / በ(፩)ና በ(፬) ተራ ፡ ቁጥር ፡ አባትነት ፡ ታልተረጋገጠ ፡ አባትነት ፡ በፍ ርድ ፡ ሊታወቅ ፡ ይችላል ። ይህም ፡ ፍርድ ፡ የሚሰጠው ፡ በእናቲቱ ፡ ላይ ፡ በጠለፋ ፡ ወይም ፡ በመደፈር ፡ ግቢረ ፡ ሥጋ ፡ የተፈጸመባት ፡ ሲሆን ፡ ነው [10] ።

፮ / በሕጋዊው ፡ አባትና ፡ (ማለት ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ (፩) መሠረት ፡ አባት ፡ የሚሆነው ፡ ሰው) ፡ ባንዲት ፡ ሴት ፡ መካከል ፡ የነበረው ፡ የጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከጋ ብቻ ፡ ውጭ ፡ የግቢረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ በተቋረጠና ፡ በ፫፻፤ና ፡ በ፫፻ ፡ ቀኖች ፡ መካከል ፡ ልጅ ፡ ከተወለደ ፡ ሕጋዊ ፡ አባት ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ አባትነቱን ፡ በውል ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ ሊያስተላልፍ ፡ ይችላል [11] ።

፯ / ለአንድ ፡ ልጅ ፡ በሕጉ ፡ መሠረት ፡ አባት ፡ የሚሆኑት ፡ ሰዎች ፡ ሁለት ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ በላይ ፡ ሲሆኑ ፡ ይህ ፡ ችግር ፡ በውል ፡ ወይም ፡ በሕጋዊ ፡ ግምት ፡ መሠረት ፡ ይወሰናል [12] ።

---

7. ቍጥር ፡ ፯፻፴፪ ። (የሌላ ፡ ሆነው ፡ ካልተገለጹ ፡ በስተቀር ፡ የግርጌ ፡ ማስረጃዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚመ መለከቱት ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግን ፡ ነው ።)
8. ቍ. ፯፻፵ (፩) ከ፯፻፵፩—፵፩ ጋር ።
9. ቍ. ፯፻፵፯(፪) ከ፯፻፵፰—፶፩ ጋር ።
10. ቍ. ፯፻፶፰ ።
11. ቍ. ፯፻፷፭ ።
12. ቍ. ፯፻፷፪ እና ፡ ፯፻፷፬ ።

ከላይ ፡ የተጠቀሱትን ፡ የአባትነት ፡ ማወቂያ ፡ ዘዴዎችን ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ጠለቅ ፡ ብለን ፡ እንመረምራለን ።

፩ / አባትነት ፡ በጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ማወቅ ።

እናትነትን ፡ ማረጋገጥ ፡ ቀላል ፡ ሲሆን ፡ (ምክንያቱም ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ ካንዲት ፡ ሴት ፡ በሥጋ ፡ መወለዱን ፡ መወሰን ፡ ቀላል ፡ ነውና ።) አባትነትን ፡ ማረጋገጥ ፡ በማንኛውም ፡ ሀገር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ታላቅ ፡ ችግር ፡ የሚፈጥር ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። ማንኛውም ፡ የተሻሻለ ፡ ሕግ ፡ ይህን ፡ ችግር ፡ ሊያቃልል ፡ የቻለው ፡ «አንድ ልጅ ፡ ሲወለድ ፡ ወይም ፡ ሲፀነስ ፡ የወለደችው ፡ ወይም ፡ የፀነሰችው ፡ ሴት ፡ ባል ፡ የነበረው ፡ ሰው ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ ነው ።» በሚል ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ሊቀርብበት ፡ በማይችል ፡ በሕግ ፡ ግምት ፡ ነው [13] ። ይህ ፡ ግምት ፡ ከጥንታዊው ፡ «አባት ፡ የሚባለው ፡ ሰው ፡ ጋብቻው ፡ ጠቅሶ ፡ የሚያመለክተው ፡ ነው ፡» ከሚለው ፡ ከሕጋዊ ፡ አባባል ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው [14] ። የኢትዮጵያዊውም ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ በዚሁ ፡ መሠረት ፡ «ልጁ ፡ የጋብቻው ፡ ሥርዓት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ከ፻፹ ፡ ቀን ፡ በሳይና ፡ ከመፋታቱም ፡ በኋላ ፡ ፫፻ ፡ ቀን ፡ ሳይሞላ ፡ የተወለደ ፡ እንደሆነ ፡ አባትና ፡ እናቱ ፡ ተጋብተው ፡ በነበሩበት ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተፀነሰ ፡ ሆኖ ፡ ይገመታል [15] ።ለዚሁ ፡ ተቃራኒ ፡ የሚሆን ፡ ማስረጃ ፡ እንዲቀርብ ፡ አይፈቀድም ። የኛ ፡ የኢትዮጵያውያንና ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሕጎች ፡ መመሳሰል ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ፩) ከላይ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ የማይቀርብበትን ፡ የሕግ ፡ ግምት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ያለውን ፡ ስፋት ፡ ፪) የዚህን ፡ ግምት ፡ ኃይል ፡ እንመረምራለን ።

፩ / የዚህ ፡ ግምት ፡ ስፋት ፤ ይህ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የአባትነት ፡ ግምት ፡ የሚያገለግለው ፡ ከጋብቻ ፡ ለተወለደ ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ በሌላም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በነበረ ፡ ግንኙነት ፡ ለተወለደ ፡ ልጅም ፡ ጭምር ፡ ነው? የውጭ ፡ ሀገር ፡ የሕግ ፡ ሊቃውንት ፡ «አንድ ፡ ልጅ ፡ በጋብቻ ፡ ጊዜ ፡ ከተወለደ ፡ አባቱ ፡ የቤትየዋ ፡ ባል ፡ ነው ፡» ብለው ፡ መወሰናቸው ፤ በጋብቻ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሚገኘውን ፡ በሴትና ፡ በወንድ ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ አብሮ ፡ የመኖርና ፡ የመተማመን ፡ ግዴታ ፡ በመመርኰዝ ፡ ነው ። ይህም ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አንድ ፡ ወንድ ፡ ካገባች ፡ ለባሏ ፡ ታማኝ ፡ ነች ፤ ባሏም ፡ እንዲሁ ፡ ሌላ ፡ ሴት ፡ ሳያውቅ ፡ ለሚስቱ ፡ ታማኝ ፡ ነው ። አብሮ ፡ መኖርም ፡ ይገባቸዋል ። እነዚህ ፡ ሁለቱ ፤ አብሮ ፡ መኖርና ፡ መተማመን ፡ በጋብቻ ፡ ምክንያት ፡ ሕጋዊ ፡ ግዴታዎቻቸው ፡ ናቸው ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ በጋብቻ ፡ መካከል ፡ ለተወለደው ፡ ልጅ ፡ አባትየው ፡ ባልየው ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ነው ። እንግዲህ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ሊቃውንት ፡ አስተያየት ፡ ይህ ፡ ነው [16] ። በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ግን ፡ «ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡» የሚባለው ፡ ሁኔታ ፡ መተማመንና ፡ አብሮ ፡ መኖር ፡ የሚባሉትን ፡ ግዴታዎች ፡ ያዘለ ፡ አይደለም ። ሆኖም ፡ አባትነትን ፡ በማወቅ ፡ በኩል ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ በሕግ ፡ ውስጥ ፡ እኩል ፡ ደረጃ ፡ ተሰጥቶታል ።

---

13. በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ልጁ ፡ የተወለደው ፡ ባልየው ፡ በሀገር ፡ የለም ፡ ተብሎ ፡ በፍርድ ፡ ከተነገረ ፡ በኋላ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ቍ. ፯፻፵፩ን ፡ ከ፯፻፵፰(፩) ፡ ጋር ፡ አስተያይ ።
14. ጂ ፡ ካርቦኛ ፡ ድርዋ ፡ ሲቪል ፡ (ፓሪስ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ፲፱፻፶፭) ፡ ቁ ፡ ኢ ፡ ቍጥር ፡ ፻፱ ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፵፩ ፡ ተመልከት ።
15. ቍ. ፯፻፵፫ ፡ ቍ. ፯፻፵፯ ፡ እና ፡ የሚከተሉት ፡ ቍጥሮች ፡ እንደሚሉት ።
16. በተራ ፡ ቍጥር ፡ ፲፬ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የካርቦኛን ፡ መጽሐፍ ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፵፫ን ፡ ከ፯፻፵፬ ፡ ጋር ፡ ተመልከት ።

«ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡» የሚፈጠረው ፡ አንድ ፡ ሰውና ፡ አንዲት ፡ ሴት፡ ልክ ፡ እንደተጋቡ ፡ ባልና ፡ ሚስት ፡ ሲኖሩ ፡ ነው [17] ። እን ዲህ ፡ ዓይነቱ ፡ አሳባች ፡ ሁኔታ ፡ ምንም ፡ በሴትዮዋና ፡ በሰውየው ፡ መካከል ፡ የመ ተማመን ፡ ግዴታ ፡ ባይፈጥርም ፡ ልክ ፡ እንደጋብቻ ፡ ሁሉ ፡ «ሰውዬው ፡ ነው ፡ ሴትዮዋን ፡ ያስፀነሳት ፡» የሚል ፡ ጥርጣሬ ፡ ይፈጥራል ። ይህን ፡ ጥርጣሬ ፡ ነው ፡ ሕጉ ፡ እንደ ፡ አባትነት ፡ ግምት ፡ ወስዶ ፡ የአባትን ፡ ማወቂያ፡ ዘዴ፡የሚያደርገው [18] ። በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ከጋብቻና ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙ ነት ፡ በተወለዱ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ ምንም ፡ ልዩነት ፡ አለመኖር ፡ አባትነትን ፡ ማሳወቅ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከላይ ፡ እንደተገለጠው ፤ አባትነትን ፡ የማሳወቂያ ፡ ዘዴዎችም ፡ ለሁለቱም ፡ ልጆች ፡ አንድ ፡ እንዲሆኑ ፡ አድርጓል ።

፪ / የዚህ ፡ የአባትነት ፡ ግምት ፡ ኃይል ፤ ይህን ፡ የአባትነት ፡ ግምት ፡ በመ ቃወም ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ሊያቀርብ ፡ የሚችል ፡ ማነው? ማስረጃውስ ፡ የሚቀር በው ፡ እንዴት ፡ ነው? ይህንንስ ፡ ለማድረግ ፡ የጊዜ ፡ ገደብ ፡ አለ ፡ ወይ? ለነዚህ ፡ ጥያቄዎች ፡ በጣም ፡ የተወሰነ ፡ መልስ ፡ በመስጠቱ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ የፈረንሳ ይን ፡ ሕግ ፡ ይመስላል [19] ።

ሀ) ይህን ፡ የአባትነት ፡ ግምት ፡ ሊቃወም ፡ የሚችለው ፡ ማን ፡ ነው? ፡— አባትነቱን ፡ በመቃወም ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ ሰው ፡ በሕግ ፡ ግምት ፡ አባት ፡ ነህ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ዓይነቱን ፡ ክስ ፡ (ታማኝ ፡ ያልሆነችው ፡) እናት ፡ ወይም ፡ ወዳጅ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ እንኳ ፡ ሊያቀርቡ ፡ አይችሉም [20] ። (የሌላን ፡ ሰው ፡ አባትነት ፡ በማመን ፡ ወይም ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ ሌላ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ሴቲቱም ፡ ሆነች ፡ ወዳጅ ፡ ወይም ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ የሕጋዊውን ፡ አባት ፡ አባትነት ፡ በመቃወም ፡ ክስ ፡ ለማቅ ረብ ፡ ይመኙ ፡ ይሆናል ። ይህን ፡ ማድረግ ፡ ግን ፡ ከላይ ፡ እንደተገለጠው ፡ ሁሉ ፡ አይችሉም ።) ይህም ፡ የተደረገበት ፡ ምክንያት ፡ የቤተሰብን ፡ ሰላምና ፡ ጸጥታ ፡ ለመጠበቅ ፡ መካሰስን ፡ ለማስወገድ ፡ ሲባል ፡ ነው ። የአባትነቱ ፡ እውነተኛነት ፡ ከቤተሰብ ፡ ሰላም ፡ ያንሳል ፡ በማለትም ፡ የተደረገ ፡ ነው ።

ለ) በሕግ ፡ ዘንድ ፡ አባት ፡ ነህ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ሊያቀ ርብ ፡ የሚችለው ፡ እንዴት ፡ ነው? የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ አውጭ ፡ ለዚህ ፡ ጥያቄ ፡ የሰጠው ፡ መልስ ፡ እንደላይኛው ፡ ጥያቄ ፡ መልስ ፡ ከመጠን ፡ በላይ ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። በሕጉ ፡ ግምት ፡ አባት ፡ ነህ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡

፩ / ከተወለደው ፡ ልጅ ፡ እናት ፡ ጋር ፡ በሕግ ፡ በተወሰነው ፡ የርግዝና ፡ ወራት ፡ ውስጥ ፡ (ልጁ ፡ ከመወለዱ ፡ በፊት ፡ በ፫፻ኛውና ፡ በ፻፹ኛው ፡ ቀኖች ፡ መካከል [21] ፡) ምንም ፡ ዓይነት ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ እንዳልነበረው ፡ ወይም፡

---

17. ቍ. ፯፻፵(፩) ፤ ፺ ፥ ከሽችኖቢች ፥ "ሕግና ፡ ባህል ፡ (ልምድ) ፡ በኢትዮጵያ" ፤ የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፳፫ ፡ ቦልዩም ፡ (፲፱፻፶፷) ፡ ገጽ ፡ ፴፱፰ ፡ ፍርዳዊ ፡ ዘይቤ ፡ የሚለውን ፡ አርእስት ።
18. ቍ. ፯፻፵፮ ።
19. ባ፲፬ ፡ ተራ ፡ ቍጥር ፡ የተጻፈውን ፡ የካርቦንን ፡ ጽሑፍ ፡ ቍ. ፺፱—፺፰ ፡ ተመልከት ።
20. ቍ. ፯፻፵ ።
21. ቍ. ፯፻፹፫ ፡ ከ፻፹፫፻ ፡ ጋር ።

፪ / የጉዳዩን ፡ አካባቢ ፡ ሁኔታዎች ፡ ማስረጃ ፡ በመመልከት ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ሲፈቅድለት ፡ አባትነቱ ፡ በጭራሽ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ ማስረዳት ፡ ይችላል [22] ። ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ገና ፡ ለገና ፡ ሴትዮዋ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ነበረኝ ፡ ብላ ፡ ሴሰኞነቷን ፡ በማመኗ ፡ ወይም ፡ ከሳሹ ፡ የተወለደው ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ አይደለም ፡ ብላ ፡ በማመን ፤ ለከሳሹ ፡ ፍርድ ፡ ቤቱ ፡ ፈቃድ ፡ ሰጥቶ ፡ አባትነቱ ፡ በጭራሽ ፡ የማይቻል ፡ መሆኑን ፡ እንዲያስረዳ ፡ ማድረግ ፡ አይችልም [23] ።

፫ / በሕጉ ፡ ግምት ፡ አባት ፡ ነህ ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ የፈቀደውን ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ሊያቀርብ ፡ የሚችለው ፤ የሴቲቱ ፡ እናትነት ፡ ራሱ ፡ አከራካሪ ፡ ሆኖ ፤ ገና ፡ በፍርድ ፡ እንዲወሰን ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ ክርክር ፡ ቀርቦ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ይህም ፡ ማለት ፡ ልጁ ፡ እናቱ ፡ ማን ፡ እንደሆነችና ፡ የልጅነቱን ፡ ሁኔታ ፡ ለማወቅ ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ እንደሆነ ፤ አባት፡ነህ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ የፈቀደውን ፡ ማስረጃ ፡ አቅርቦ ፡ አባትነቱን ፡ ሊክድ ፡ ይችላል [24] ።

ሐ) በሕጉ ፡ ግምት ፡ አባት፡ነህ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ አባትነቱን ፡ በመካድ ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ መቼ ፡ ነው? መልሱ ፡ አሁንም ፡ የተወሰነ ፡ ነው ። ይህን ፡ ለማድረግ ፡ የሚችለው ፡ የተባለው ፡ ልጅ ፡ በተወለደ ፡ በ፻፹ ፡ ቀን ፡ ወይም ፡ የተባለው ፡ ልጅ ፡ እናቱ ፡ ማን ፡ እንደሆነች ፡ ለማወቅ ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ ክስ ፡ አቅርቦ ፡ ጉዳዩ ፡ በፍርድ ፡ ቤት ፡ በተወሰነ ፡ በ፻፹ ፡ ቀን ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

<u>መደምደሚያ ፤</u>

በኢትዮጵያ ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ የተመለከተው ፡ የአባትነት ፡ ግምት ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ ለተወለዱ ፡ ልጆች ፡ የአባትነት ፡ ማሳወቂያ ፡ ሆኖ ፡ ስለሚያገለግል ፡ የዚህ ፡ ሕግ ፡ ስፋት ፡ ታላቅ ፡ ነው ። ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችለው ፡ ሰው ፡ የሚያቀርብበት ፡ ጊዜና ፡ የሚያቀርብበት ፡ መንገድ ፡ የተወሰኑ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የዚህ ፡ የሕግ ፡ ግምት ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ <u>ኃይል</u> ፡ አለው ።

## <u>፪ ፤ አባትነትን ፡ ስለማወቅ ፤</u>

ከጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ሳይሆን ፡ እንዲሁ ፡ ጽናት ፡ ከሌለው ፡ ግንኙነት ፡ የሚወለዱ ፡ ልጆች ፡ ሕጋዊ ፡ መተሳሰር ፡ ያላቸው ፡ ከእናታቸው ፡ ብቻ ፡ ነው ። እነዚህ ፡ ልጆች ፡ አባቶቻቸው ፡ በግል ፡ ፈቃዳቸው ፡ አቅፈው ፡ አባትነታቸውን ፡ ካላወቁላቸው ፡ ወይም ፡ የጉድፈቻ ፡ አባት ፡ ካላገኙ ፡ አባት ፡ እንዳላቸው ፡ አይቆጠሩም [25] ። <u>አባትነትን ፡ ማወቅ ፡ ማለት ፡</u> አንድ ፡ ሰው ፡ በፈቃዱ ፡ የአንድ ፡ ልጅ ፡ «አባት ፡ ነኝ ፡» ብሎ ፡ ከማወቁ ፡ የተነሣ ፡ አባትነቱን ፡ ሲያረጋግጥ ፡ ነው [26] ። በዚህ ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ አባትነት ፡ የሚረጋገጥለት ፡ ሕጋዊ ፡ አባት ፡ የሌለው ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የዚህ ፡ ዐይነቱ ፡ አባት

---

22. ቍ. ፯፻፹፩—፹፯ ። በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ የሚቀርብ ፡ የነገሩ ፡ አካባቢ ፡ ማስረጃ ፡ የሚከተሉትን ፡ ሊይዝ ፡ ይችላል ፤ ለምሳሌ ፡ ፈጽሞ ፡ የማይመስል ፡ መልክ ፡ (ከፈረንጅ/ነጭ) ፡ ወላጆች ፡ የተወለደ ፡ ጥቁር ፡ ልጅ) ፡ ሊፈጸም ፡ (ሊሆን) ፡ የማይቻል ፡ ለምሳሌ ፡ መካንነት ፡ ወይንም ፡ የማይመስል ፡ የደም ፡ ምርመራ ።
23. ቍ. ፯፻፹፰ ።
24. ቍ. ፯፻፹፱ ፡ ከ፯፻፸፪ ፡ ጋር ።
25. ቍ፣ ፯፻፸፭(፪) ፡ ወይንም ፡ አባትነት ፡ በፍርድ ፡ ካልተነገረ ፡ በስተቀር ፡ (ገቅ ፡ ብለሀ ፡ ተመልከት)
26. ቍ. ፯፻፵፯—፵፰ ።

ነት ፡ ማወቅ ፡ በጉዲፈቻ ፡ ከሚፈጠረው ፡ አባትነት ፡ ባንድ ፡ ታላቅ ፡ ረገድ ፡ ይለያል [27] ። የአንድን ፡ ሰው ፡ የጉዲፈቻ ፡ አባት ፡ መሆን ፡ ዘመዶቹ ፡ የተቃወሙት ፡ እንደሆነ ፡ የሰውየው ፡ የጉዲፈቻ ፡ አባትነት ፡ ዘመዶቹን ፡ አይመለከታቸውም ። ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ በትክክለኛው ፡ መንገድ ፡ ካረጋገጠ ፡ ዘመዶቹ ፡ ቢወዱም ፡ ባይወዱም ፡ የሰውየው ፡ አባትነት ፡ የሚያስከትለው ፡ ሁሉ ፡ እነርሱንም ፡ ይመለከታቸዋል [28] ። (ከታች ፡ ተመልከት) ። ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ «ስለ ፡ አባትነት ፡ ማወቅ ፡» ከዚህ ፡ ሥር ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ፯ ፡ ነጥቦች ፡ እንመረምራለን ።

፩ / ልጅን ፡ አቅፎ ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ሲል ፡ አባትነቱን ፡ ለማወቅ ፡ የሚችል ፡ ማነው? በመታቀፍ ፡ ልጅነቱንስ ፡ ሊያሳውቅ ፡ የሚችል ፡ ማነው?

ሀ) ይበልጡን ፡ ጊዜ ፤ ልጅን ፡ አቅፎ ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ሲል ፡ የሚችለው ፡ አባት ፡ ነህ ፡ በመባል ፡ የተጠረጠረው ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ሞቶ ፡ ወይም ፡ ሐሳቡን ፡ መግለጽ ፡ የማይችል [29] ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባባት ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ የወንድ ፡ አያት ፡ በሞተው ፡ ወይም ፡ ሐሳቡን ፡ ለመግለጽ ፡ ባልቻለው ፡ ሰው ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተባለውን ፡ ልጅ ፡ ማወቅ ፡ ይችላል [30] ።

ለ) ይበልጡን ፡ ጊዜ ፡ በመታቀፍ ፡ አባትነቱ ፡ ሊታወቅለት ፡ የሚችል ፡ በሕይወት ፡ ያለ ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የሞተ ፡ ልጅ ፡ ልጆች ፡ ወልዶ ፡ ትቶ ፡ ካልሞተ ፡ አባትነቱ ፡ ሊታወቅለት ፡ አይችልም [31] ።

፪ ፡ የማወቁ ፡ አሠራር ፡ ፎርም ፤

ሀ) አባትነትን ፡ ማወቅ ፡ በጽሑፍ ፡ ሆኖ ፡ የ፪ ፡ ምስክሮች ፡ ፊርማ ፡ በጽሑፍ ፡ ላይ ፡ መኖር ፡ አለበት [32] ።

ለ) በፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ በተደረገ ፡ በልዩ ፡ የውክልና [33] ፡ ሥልጣን ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ የኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አባትነቱን ፡ የሚያውቅ ፡ ሰው ፡ የማወቅ ፡ ቃሉን ፡ ራሱ ፡ መስጠት ፡ አለበት [34] ።

፫ / አባትነትን ፡ መቀበል ፡ ስለማስፈለጉ ፤

አባትነቱን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሲያውቅ ፡ ይህን ፡ አባትነት ፡ የልጁ ፡ እናት ፡ ወይም ፡ እናቲቱ ፡ ሞታ ፡ እንደሆነ ፡ (ወይም ፡ ሐሳቧን ፡ ለመግለጽ ፡ የማትችል ፡ የሆነች ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡) በእናት ፡ በኩል ፡ ያለ ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ አያት [35] ፡ ወይም ፡ የልጅ ፡ ሞግዚት [36] ፡ ካልተቀበሉትና ፡ ፈቃድ ፡ ካልሰጡ ፡ አይጸናም ።

---

27. ቍ፣ ፯፻፵፭—፯፻፵፮ ። እንዲሁም ፡ ቍ፣ ፯፻፵፫ ፡ ተመልከት ።
28. ተቀባዩ ፡ የቀለብ ፡ መስጠትና ፡ ወይም ፡ የውርስ ፡ መብቶችን ፡ በነርሱ ፡ ላይ ፡ ያገኛል ።
29. ዘላቂ ፡ የሆነ ፡ እብደት ፡ ወይም ፡ እራሱን ፡ ማጣት ፡ (በድንገት) ፡ ዓይነት ፡ ወይም ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፵፬ ፡ እንደተመለከተው ፡ በጻፎች ፡ የሰውዬው ፡ መጥፋት ፡ የተነገረ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ።
30. በቍጥር ፡ ፯፻፵፱ ፡ አነጋገር ።
31. ቍ. ፯፻፶፩ ።
32. ቍ. ፯፻፶፪(፩) ከ፹፻፸፱ ፡ እና ፡ ፲፯፻፳፰ ፡ ጋር ። ቍጥር ፡ ፯፻፶፪(፪) ፡ ግን ፡ ደንበኛ ፡ ማወቅ ፡ እንደነበር ፡ በተለየ ፡ አኳኋን ፡ የማስረዳትን ፡ ዘዴ ፡ የሚመለከት ፡ ነው ። (በግልጽ ፡ የታወቀ ፡ ሥራ) ።
33. ቍ. ፯፻፶፪(፪) ከ፲፯፻፳፯(፩) ጋር ።
34. ቍ. ፯፻፶፪(፩) ።
35. በቍ. ፯፻፶፩ ፡ አነጋገር ።
36. ስለዚህ ፡ በቍ. ፯፻፲ (መ—ሰ) ፡ ከተጠቀሱት ፡ ዘመዶች ፡ አንዱ ፡ ይሆናል ።

ልጁ ፡ ለአካለ ፡ መጠን ፡ አድርሶ ፡ እንደሆንና ፡ ሞግዚት ፡ የሌለው ፡ እንደሆን ፡ እርሱም ፡ በተጨማሪ ፡ የሰውየውን ፡ አባትነት ፡ መቀበል ፡ አለበት [37] ። የልጁ ፡ እናትም ፡ ትሁን ፡ ወይም ፡ ወላጆቿ ፡ ወይም ፡ አካለ ፡ መጠን ፡ ያደረሰው ፡ ልጅ ፡ የዚያን ፡ ሰው ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ማለት ፡ ሰምተው ፡ በአንድ ፡ ወር ፡ ውስጥ ፡ ሳይቃወሙ ፡ ከቆዩ ፡ የሰውየውን ፡ አባትነት ፡ እንደ ፡ ተቀበሉት ፡ ይቆጠራል [38] ። ይህም ፡ ማለት ፡ ዝም ፡ ማለታቸው ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ የሰውየውን ፡ አባትነት ፡ እንደ ፡ ተቀበሉ ፡ ያስቆጥራቸዋል ፡ ማለት ፡ ነው ። እነዚህ ፡ አባትነትን ፡ ለማወቅ ፡ የሚያስፈልጉት ፡ ሥርዓቶች ፡ አባትነት ፡ በማወቅ ፡ ከመረጋገጡ ፡ በፊት ፡ እንደሌሎች ፡ የአባትነት ፡ ማወቂያ ፡ መንገዶች ፡ ሁሉ ፡ መጀመሪያውኑ ፡ እናትነት ፡ ባንድ ፡ ልጅ ፡ በሥጋ ፡ መወለድ ፡ ምክንያት ፡ ተረጋግጧል ፡ በሚል፡ ስሜት ፡ ላይ ፡ የተመሠረቱ ፡ ናቸው ። በተጨማሪም ፡ አባትነቱን ፡ በማወቅ ፡ የሚያረጋግጥ ፡ ሁሉ ፡ እውነተኛ ፡ አባት ፡ መሆኑን ፡ የልጁም ፡ ጥቅም ፡ እንዲታሰብ ፡ ማድረጉን ፡ ያሳያል ። ይህም ፡ ማለት ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ እየተነሣ ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ቢል ፡ አባትነቱ ፡ በወላጆቹ ፡ ዘንድም ፡ ሆነ ፡ በዘመዶቿ ፡ ወይም ፡ በልጁ ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነት ፡ ካላገኘ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፤ የዚህም ፡ ውጤት ፡ እውነተኛ ፡ አባት ፡ ብቻ ፡ አባትነቱን ፡ በማወቅ ፡ እንዲያረጋግጥ ፡ ማድረግ ፡ ነው ።

፬ / <u>አባትነትን ፡ ለመሻርና ፡ ለማስወገድ ፡ ስለ ፡ መሞከር ፤</u>

ልጆች ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ያላቸውን ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ አጽንቶ ፡ ለመጠበቅ ፡ ሲባል ፡ አባትነቱን ፡ በማወቅ ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፤ የለም ፡ አባት ፡ አይደለሁም ፡ ብሎ ፡ ለሚጸጸት ፡ አባት ፡ ሕጋዊ ፡ ድጋፍ ፡ የለውም ፤ ቢኖረውም ፡ በጣም ፡ ትንሽ ፡ ነው ።

ሀ) በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ አባትነት ፡ <u>የሚሻር</u> ፡ አይደለም ። አንድ ፡ ሰው ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ካወቀ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ መልሶ ፡ አባት ፡ አይደለሁም ፡ ሊል ፡ አይችልም ። (ግን ፡ የአባትነት ፡ ማወቅ ፡ በኑዛዜ ፡ ውስጥ ፡ የተገለጠ ፡ እንደሆን ፡ ኑዛዜው ፡ ሊሻርና ፡ ኑዛዜነቱ ፡ ሊቀር ፡ ስለሚችል ፡ አባትነቱም ፡ አብሮ ፡ ሊሻር ፡ ይችላል [39] ። )አባት ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ አባትነቱን ፡ ሊሽር ፡ የሚችል ፡ ለአቅመ ፡ አዳም ፡ ያልደረሰ ፡ ልጅ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህም ፡ ልጅ ፡ አባትነቱን ፡ ሊሽር ፡ የሚችለው ፡ ለአቅመ ፡ አዳም ፡ ካደረሰ ፡ በኋላ ፡ ባለው ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ነው [40] ። ከዚያ ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ሊሽር ፡ አይችልም ።

ለ) አባት ፡ ነኝ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ አባትነቱን ፡ ሊያውቅ ፡ የቻለው ፡ <u>በፈቃዱ ፡ ሳይሆን</u> ፡ በኃይል ፡ ተገዶ ፡ እንደሆነ ፡ የአባትነቱን ፡ ማወቅ ፡ ሊሽር ፡ ይችላል [41] ። ስለሆነም ፡ አንድ ፡ ሰው [42] ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ መልሶ ፡ ተሳስቼ ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ ተንኮል ፡ ተመርቼ ፡ ነው ፡ አባት ፡ መሆኔን ፡ ያወቅሁት ፡ ብሎ ፡ አባትነቱን ፡ ሊሽር ፡ <u>አይችልም</u> ። አንድ ፡ ሰው ፡ በስሕተት ፡ ወይም ፡ በሰው ፡ ተን

---

37. ቍ. ፯፻፵፯ ።
38. ቍ. ፯፻፵፰ ።
39. ቍ. ፰፻፶፱(፪) ።
40. ቍ. ፯፻፶፭ ።
41. ቍ. ፯፻፶፩(፩) ፡ ከ፯፻፶፪ ፡ ጋር ።
42. ቍ. ፯፻፶፮(፪) ፡ ከ፯፻፶፭—፯፻፶፱ ፡ ጋር ።

ኮል ፡ ምክንያት ፡ ያረጋገጠውን ፡ አባትነት ፡ ሊሽር ፡ የሚችለው ፡ በተጨማሪ ፡ ፍጹም ፡ አባት ፡ ሊሆን ፡ አለመቻሉን ፡ ያረጋገጠ ፡ እንደሆነ ፡ ነው [43] ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ እንግዲህ ፡ በማትታመን ፡ ወዳጁ ፡ ተታሎ ፡ የአንድን ፡ ልጅ ፡ አባትነት ፡ በፈቃዱ ፡ ያወቀ ፡ ሁሉ ፡ በሕግ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ ማድረግ ፡ አይችልም ፤ አባትነቱ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ይኖራል ።

፭ / ሁለት ፡ ሰዎች ፡ የአንድ ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ሲያውቁ ፤

ከላይ ፡ ከ፩ ፡ እስከ ፡ ፬ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ተራ ፡ ቍጥሮች ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ አባቱ ፡ ታውቆ ፡ ከተረጋገጠለት ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ መጥቶ ፡ አባትህ ፡ ነኝ ፡ ሲል ፡ አባትነቱን ፡ ቢያውቅለት ፡ የኋለኛው ፡ አባትነት ፡ አይጸናም [44] ።

፮ / የአንድን ፡ ሰው ፡ የአባትነት ፡ ማወቅ ፡ ስለ ፡ መቃወም ፤

አንድ ፡ ሰው ፡ የአንድ ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ አባትነቱን ፡ ሲያውቅ ፡ አባትነቱን ፡ መቃወም ፡ ወይም ፡ ፍጹም ፡ መካድ ፡ የሚቻለው ፡ በሚከተሉት ፡ ሁኔታዎች ፡ ነው ።

ሀ) ማንም ፡ በጉዳዩ ፡ ያገባኛል ፡ የሚል ፡ ሰው ፡ ይህም ፡ ማለት ፡ ጥቅሙን ፡ የሚነካበት ፡ ዘመድ ፡ ሁሉ ፡ አባትነቱን ፡ ያወቀው ፡ ሰው ፡ የተፈቀደለት ፡ ሰው ፡ አይደለም ፡ (ቍጥር ፡ ፩ን ፡ ከላይ ፡ ተመልከት ፡) ወይም ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ አባትነቱን ፡ መቀበል ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ አባትነቱን ፡ አልተቀበለም ፡ (ቍጥር ፡ ፫ን ፡ ተመልከት) ፡ ወይም ፡ ሕጉ ፡ እንደሚለው ፡ አባትነቱ ፡ በጽሑፍ ፡ አልሰፈረም ፡ በተጨማሪም ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ባዩ ፡ ሳይሆን ፡ በርሱ ፡ ስም ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ነው ፡ አባትነቱን ፡ ያረጋገጠው ፡ (ቍጥር ፡ ፪ን ፡ ከላይ ፡ ተመልከት) ፡ ወይም ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ባዩ ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ የሚለው ፡ ልጅ ፡ መጀመሪያውኑ ፡ የተረጋገጠ ፡ አባት ፡ አለው ፡ (ቍጥር ፡ ፭ን ፡ ከላይ ፡ ተመልከት ፡) በማለት ፡ አባትነትን ፡ መቃወም ፡ ይቻላል ።

ለ) ከላይ ፡ በቍጥር ፡ ፬(ለ) በተመለከተው ፡ መሠረት ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ባዩ ፡ ራሱ ፡ ብቻ [45] ፡ አባትነቱን ፡ ሊክድ ፡ ወይም ፡ ሊቃወም ፡ ይችላል ።

፯ / ልጅን ፡ በማወቅ ፡ የሚረጋገጥ ፡ አባትነት ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ እንደምን ፡ እንደሚገመት [46] ፤

ሀ) አባትነትን ፡ ማወቅ ፡ በልጅና ፡ ባባት ፡ መካከል ፡ ያልነበረን ፡ መተሣሠር ፡ አሁን ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ የሚፈጥር ፡ ሕጋዊ ፡ ተግባር ፡ ነው ፡ ወይስ ፡ አባትነት ፡ መጀመሪያውኑ ፡ (አባትነቱ ፡ ከመረጋገጡም ፡ በፊት ፡) መኖሩን ፡ (በማመን ፡) የማስረጃ ፡ ዘዴ ፡ ነው? ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡ አባትነቱ ፡ ሳይታወቅለት ፡ በፊት ፡ ውርስ ፡ ኖሮ ፡ እንደሆነ ፡ አባትነቱ ፡ ከተረጋገጠለት ፡ በኋላ ፡ "ካለፈው ፡ ውርስ ፡ ድርሻዬ ፡ አሁን ፡ ይሰጠኝ" ፡ ብሎ ፡ ሊጠይቅ ፡ ይችላልን? [47] መልሱ ፡ ቀላል ፡

43. ለምሳሌ ፡ መካን ፡ መሆኑን ፡ በማረጋገጥ ።

44. ቍ. ፯፻፵፯ ።

45. ቍ. ፯፻፵፰(፩) ፡ አስተያይ ።

46. በተራ ፡ ቍ ፡ ፲፱ ፡ የተገለጸውን ፡ የካርቦኒየን ፡ ጽሑፍ ፡ ቍጥር ፡ ፻፷፯ ፡ እና ፡ ቢሞቴን ፡ ላ ፡ ናቱሬል ፡ ዡሪዲክ ፡ ድ ፡ ላ ፡ ሸኮሳንስ ፡ ዴ ፡ ኤንፋ ፡ ናቱሬል ፡ ፊል ፡ (እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ፲፱፻፴፩ ፡ ዓ ፡ ም) ።

47. ለምሳሌ ፡ በቍ. ፯፻፵፱—፯፻፶፩ ፡ ስር ፡ የወራሽነት ፡ ጥያቄ ። ይህ ፡ የተጨበጠ ፡ (የተገኘ) ፡ ውርስን ፡ በማናጋት ፡ የማጭበርበር ፡ ሥራን ፡ የሚያበረታታ ፡ ነው ።

አይደለም ። አባትነትን ፡ ማወቅ ፤ ጥንትም ፡ አባትነት ፡ መኖሩን ፡ ለማሳየት ፡ በፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ መወለድ ፡ በሚናገረው ፡ በምዕራፍ ፡ ፰ ፡ ክፍል ፡ ፫ ፡ ውስጥ ፡ ከተዘረዘሩት ፡ ማስረጃዎች ፡ አንዱ ፡ ሆኖ ፡ አይገኝም [48] ። ሆኖም ፡ አባትነትን ፡ ማወቅ ፡ በመወለድ ፡ ምክንያት ፡ ሕጋዊ ፡ መተሣሰርን ፡ ከሚፈጥሩት ፡ አንዱ ፡ ነው [49] ። ግን ፡ በቍጥር ፡ ፯፻፵፱(፪) ውስጥ ፡ እንደተመለከተው ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ባዩ ፤ አባት ፡ ነኝ ፡ ማለቱ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት ፡ መሻቱ ፡ አስፈላጊ ፡ አይደለም ፤ ሆኖም ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤትን ፡ ለማስከተል ፡ መሻት ፡ ግን ፡ «የሕጋዊ ፡ ተግባር ፡» አስፈላጊ ፡ ጠባይ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ አባትነትን ፡ ማወቅ ፡ «በእምነት ፡ መቀበል ፡» የሚባለውን ፡ የማስረጃ ፡ ዘዴን ፡ ስለሚመስል ፤ ጥንት ፡ የነበረውን ፡ አባትነት ፡ ለማስረዳት ፡ በከፊል ፡ የሚያስችል ፡ ዘዴ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ «ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡» ውጤት ፡ ያመጣል ፡ ለማለት ፡ ያስደፍረናል ። ይህ ፡ አስተያየት ፡ ማንም ፡ ሰው ፡ ከሚያስበው ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ ነው ። አንድ ፡ ሰው ፡ ያንድ ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ አይደለም ፡ ወይም ፡ አባት ፡ ነው ፡ ከተባለ ፡ ከጥንቱ ፡ ከፅንሰቱ ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አባትነቱ ፡ ከተረጋገጠበት ፡ ቀን ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ አባት ፡ ነው ፡ ሊባል ፡ አይቻልም ። በሰው ፡ ሠራሽ ፡ የሚፈጠረው ፡ የጉዲፈቻ ፡ አባትነት ፡ (የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፶፯ ፡) ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሶ ፡ የሚሠራ ፡ ሕጋዊ ፡ ተግባር ፡ የለውም ፤ በጉዲፈቻ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ያንድ ፡ ልጅ ፡ አባት ፡ የሚሆነው ፡ የጉዲፈቻ ፡ ሥርዓት ፡ ከተፈጸመበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ላንድ ፡ ሰው ፡ ልጅ ፡ በጉዲፈቻ ፡ አባት ፡ መሆን ፡ (አዲስ ፡ ሁኔታን ፡ መፍጠር ፡) የራስን ፡ ልጅ ፡ የኔ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ አቅፎ ፡ አባትነትን ፡ ማወቅ ፡ (ጥንትም ፡ የነበረን ፡ ሁኔታ ፡ እንዲቀጥል ፡ ከማድረግ) ፡ እጅግ ፡ የተለየ ፡ ነው ።

ለ) ይህ ፡ አባትነትን ፡ የማወቅ ፡ ሕጋዊ ፡ ተግባር ፡ የአንድን ፡ ሰው ፡ የብቻ ፡ ተግባር ፡ ወይም ፡ የሁለትን ፡ ወይም ፡ ከሁለት ፡ በላይ ፡ የሆኑን ፡ ሰዎች ፡ መፈቃቀድ ፡ የሚጠይቅ ፡ ስምምነትን ፡ የሚመስል ፡ ተግባር ፡ ነው? አባትነት ፡ ተቀባይ ፡ እንዲኖረው ፡ ያሻል? (ቍጥር ፡ ፫ን ፡ ከላይ ፡ ተመልከት ፡) በሚለው ፡ አስተያየት ፡ ስንመለከተው ፡ እንዲህ ፡ ዐይነቱ ፡ ያባትነት ፡ ማወቂያ ፡ ዘዴ ፡ ስምምነትን ፡ ይመስላል ። ይህ ፡ ከሆነ ፡ እንግዲህ ፡ አባትነቱን ፡ የተቀበለች ፡ ሴት ፡ የተቀበለችው ፡ በኃይል ፡ ተገዳ ፡ እንደሆነ ፡ አባትነቱን ፡ ልትሽር ፡ ትችላለች ። (ከላይ ፡ ካለው ፡ ከቍጥር ፡ ፯ ፡ ጋር ፡ ያወዳድሯል ፡) በይበልጥ ፡ ደግሞ ፡ በኑዛዜ ፡ የተረጋገጠ ፡ አባትነት ፡ በግልጽ ፡ ወይም ፡ በሁኔታ ፡ በሚረጋገጥ ፡ ተቀባይነት ፡ ካልተደገፈ ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፤ አይጸናም ፡ ማለት ፡ ነው ።

## ፫ / በፍርድ ፡ ስለሚደረግ ፡ የአባትነት ፡ ማወቅ ፤

አንድ ፡ ልጅ ፡ ከላይ ፡ በተመለከቱት ፡ ክፍል ፡ ፩ ፡ (አባትነትን ፡ በጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በነበረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ስለማወቅ) ፡ ወይም ፡ ክፍል ፡ ፪ ፡ (ልጅን ፡ ተቀብሎ ፡ አባትነት ፡ ስለማወቅ ፡) መሠረት ፡ አባቱ ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ ሊታወቅለት ፡ ካልተቻለ ፡ በክፍል ፡ ፫ ፡ መሠረት ፡ አባቱ ፡ በፍርድ ፡ ሊታወቅለት ፡

48. ቍ፡ ፯፻፶፱—፸፪ ፤ የመወለድ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ወይንም ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ ወይንም ፡ ግልጽ ፡ የሆነ ፡ መታወቅ ።

49. ቍ. ፯፻፶፩ ።

ይችላል ። ይህም ፡ ሊሆን ፡ የሚችለው ፡ እናትየው ፡ በፀነሰችበት ፡ ወቅት ፡ የጠለፋ ፡ ወይም ፡ የመደፈር ፡ ተግባር ፡ ተፈጽሞባት ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ነው [50] ።
ከዚህም ፡ የሚከተለው ፤

፩ / የመደፈር ፡ ወይም ፡ የጠለፋ ፡ ሥራ ፡ ተፈጽሞባት ፡ የልጅ ፡ አባት ፡ ማን ፡ እንደሆነ ፡ የምታውቅ ፡ ሴት ፡ የልጁ ፡ አባት ፡ ይረጋገጥልኝ ፡ ብላ ፡ ክስ ፡ ልታቀርብ ፡ አትችልም ።

፪ / የ«ጠለፋ ፡» ወይም ፡ የ«መደፈር ፡ ሥራ ፡ መፈጸም ፡» የሚባሉት ፡ ቃላት፡ በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ ያልተገለጹ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የነዚህ ፡ ቃላት ፡ ትርጉም ፡ በወንጀለኛ ፡ መቅጫው ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ እንደተገለጸው ፡ መውሰድ ፡ አለብን [51] ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ አባትነት ፡ በፍርድ ፡ የሚረጋገጠው ፡ በጠለፋ ፡ ወይም ፡ በመደፈር ፡ የተፈጸመ ፡ ሥራ ፡ ከሚያስከትለው ፡ የወንጀል ፡ ቅጣት ፡ በኋላ ፡ ነው ። ጠላፊን ፡ ወይም ፡ ደፋሪን ፡ በወንጀል ፡ ለማስቀጣትና ፡ የልጅን ፡ አባት ፡ በፍርድ ፡ ለማወቅ ፡ የሚቀርቡት ፡ ክሶች ፡ ተጣምረው ፡ ባንድነት ፡ ሊቀርቡ ፡ ይችላሉ [52] ።

፫ / አባትነት ፡ በፍርድ ፡ እንዲረጋገጥ ፡ ክስ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ «የርግዝናን ፡ ወራት ፡» ወይም ፡ አባትነቱ ፡ ሊረጋገጥለት ፡ የቀረበው ፡ ልጅ ፡ የተፀነሰበትን ፡ ጊዜ ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፹፫ ፡ በሚወስነው ፡ አምሳያ ፡ መወሰን ፡ ይቻላል ።

«አባትነትን ፡ በፍርድ ፡ ማወቅ ፡» ከዚህ ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ ሁኔታዎች ፡ ያዘለ ፡ ነው [53] ።

፩ / አባትነት ፡ በፍርድ ፡ ይታወቅልኝ ፡ ሲል ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የሚችል ፡ ማነው? በጠቅላላ ፡ አነጋገር ፡ ይህን ፡ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ የምትችል ፡ የጠለፋ ፡ ወይም ፡ የመደፈር ፡ ሥራ ፡ የተፈጸመባት ፡ ልጅ ፡ የወለደችው ፡ ሴት ፡ ብቻ ፡ ነች ። እናቲቱ ፡ ሞታ ፡ ወይም ፡ ሐሳቧን ፡ ለመግለጽ ፡ ያልቻለች ፡ እንደሆነ ፡ የልጁ ፡ ሞግዚት ፡ ክሱን ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

፪ / ክሱን ፡ ማቅረብ ፡ የሚቻለው ፡ መቼ ፡ ነው? ክሱን ፡ ማቅረብ ፡ የሚቻለው ልጁ ፡ ከተወለደ ፡ ወይም ፡ በጠለፋ ፡ ወይም ፡ በድፍረት ፡ ስለ ፡ ተፈጸመው ፡ ሥራ ፡ ክስ ፡ ቀርቦ ፡ ጥፋተኛው ፡ ቅጣት ፡ ከተወሰነበት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ነው ።

፫ / መከላከያ ፡ ክሱ ፡ የቀረበበት ፡ ጠላፊ ፡ ወይም ፡ ደፋሪ ፡ የተባለውን ፡ የጠለፋ ፡ ወይም ፡ የድፍረት ፡ ወንጀል ፡ በሴትየዋ ፡ ላይ ፡ በፈጸምኩባት ፡ ወቅት ፡ ላስፀንሳት ፡ አልችልም ፡ ነበር ፡ ሲል ፡ ያለመቻሉን ፡ ሁኔታ ፡ ካረጋገጠ ፡ (ለምሳሌ ፡ በመካንነት ፡ የተነሣ ፡ ሴትዮዋን ፡ ላስፀንሳት ፡ አልችልም ፡ ብሎ ፡ መካንነቱን ፡ ካረጋገጠ) ፡ ለክሱ ፡ ፍጹም ፡ መከላከያ ፡ ይሆነዋል ።

፬ / አባትነት ፡ በዳኛ ፡ ፍርድ ፡ ይታወቅልኝ ፡ ሲባል ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ የሚቻለው ፡ በጠለፋ ፡ ወይም ፡ በድፍረት ፡ ሥራ ፡ ከተፈጸመ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙ

---

50. ቍ. ፯፻፶፰ ።
51. የወንጀለኛ ፡ መቅጫ ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፭፻፹፱ ፡ እና ፡ ፭፻፺፱ ።
52. ፊሊፕ፡ ግራቨን ፡ "የወንጀልና ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ግምራ ፡ ክስ" ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት፡ ፩ኛ ፡ ቮልዩም ፡ ፩ (፲፱፻፷፬) ፡ ገጽ ፡ ፻፭—፱ ፡ ተመልከት ።
53. ቍ. ፯፻፶፱—፷፩ ፡ ተመልከት ።

ነት ፡ የተነሣ ፡ ልጅ ፡ ሲወለድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። በሌላ ፡ ምክንያት ፡ የተነሣ ፡ አባት ነት ፡ በፍርድ ፡ ይረጋገጥልኝ ፡ በማለት ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ። እንዲህም ፡ ሲባል ፡ ከላይ ፡ በክፍል ፩ና ፡ ፪ ፡ በተዘረዘሩት ፡ ዘዴዎች ፡ መሠረት ፡ አባትነት ፡ መታወቁን ፡ ለማስረዳት ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፡ አይቻልም ፡ ማለት ፡ አይደለም ። ዋናው፡ ሐሳብ ፡ አባትነትን ፡ በፍርድ ፡ ማወቅ ፡ የሚባለው ፡ የአባትነት ፡ ማወቂያ ፡ ዘዴ ፡ የሚያገለግለው ፡ በጠለፋ ፡ ወይም ፡ በድፍረት ፡ ሥራ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ ሲወለድና ፡ የልጁን ፡ አባት ፡ በሌላ ፡ ዘዴ ፡ ማወቅ ፡ ሳይ ቻል ፡ ሲቀር ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ለማለት ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አንድን ፡ ሴት ፡ በማባበል ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ የወለደች ፡ እንደሆነ ፡ የልጇ ፡ አባት ፡ በዳኝነት ፡ ይታወቅልኝ ፡ ብላ ፡ ክስ ፡ ልታቀርብ ፡ አትች ልም [54] ። ይህ ፡ እንዲህ ፡ የሆነበትን ፡ ምክንያት ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ መግቢያ ፡ ላይ ፡ አስረድተናል ።

፫ / አባትነት ፡ በዳኛ ፡ ፍርድ ፡ ሲታወቅ ፡ የሚያስከትለው ፡ ሕጋዊ ፡ ውጤት፤

አባትነትን ፡ በፍርድ ፡ ማሳወቅ ፡ ያንድን ፡ ሰው ፡ ወንጀለኛ ፡ ጥፋት ፡ የመ ቅጫ ፡ አንድ ፡ ዘዴ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ አባትነት ፡ በክፍል ፡ ፩ና ፡ ፪ ፡ ሲረጋገጥ ፡ ከሚያስከትለው ፡ ውጤት ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በሚከተለው ፡ ረገድ ፡ ይለያያል ። በዳኛ ፡ ፍርድ ፡ አባት ፡ ነህ ፡ የተባለው ፡ ጠላፊ ፡ ወይም ፡ ደፋ ሪው ፡ ልጁን ፡ የመርዳት ፡ ሕጋዊ ፡ ግዴታ ፡ ሲኖርበት ፡ አባትህ ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ አባቱን ፡ የመርዳት ፡ ሕጋዊ ፡ ግዴታ ፡ የለበትም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ልጁ ፡ ካደገ ፡ በኋላ ፡ በፍርድ ፡ ታውቆልኝ ፡ ማሳደጊያ ፡ የከፈለልኝን ፡ አባቴን ፡ አልረዳም ፡ ሊል ፡ ይችላል ። አንድ ፡ ልጅ ፡ በዳኛ ፡ ፍርድ ፡ የታወቀለትን ፡ አባት ፡ የመርዳት ፡ ግዴታ ፡ የለበትም [55] ።

፬ ፤ አባትነትን ፡ በውል ፡ ስለማስተላለፍ ፤

በሕግ ፡ ሲታውንት ፡ ዘንድ ፡ በተለመደው ፡ አነጋገር ፡ የሰው ፡ መብቶች ፡ እንደ ፡ ንግድ ፡ ዕቃ ፡ በስምምነት ፡ የሚወሰኑ ፡ አይደሉም ። በሕግ ፡ የተወሰኑ ፡ ስለሆኑ ፡ ሊሸጡ ፡ ወይም ፡ ሊለወጡ ፡ አይችሉም ። ይህ ፡ የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሊቃው ንት ፡ አነጋገር ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕግና ፡ ባሕል ፡ የጠበቀ ፡ መሠረት ፡ ያለው ፡ አነጋ ገር ፡ አይደለም [56] ። የአንድ ፡ ሰው ፡ ጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከንዲት ፡ ሴት ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ ያለ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት [57] ፡ ከፈረሰ ፡ ወይም ፡ ካቆመ ፡ ከ፫፻ ፡ ቀኖች ፡ በኋላ ፡ ልጅ ፡ የተወለደ ፡ እንደሆነ ፡ ሕጋዊ ፡ አባት ፡ የሆነው ፡ አባት ነቱን ፡ ለሌላ ፡ ሰው ፡ በስምምነት ፡ ሊያስተላልፍ ፡ ይችላል ። [58]

፩ / ልጁ ፡ የተወለደው ፡ ጋብቻው ፡ ከፈረሰ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የግ ብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነቱ ፡ ከቆመ ፡ ከ፪፻፲ ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ መሆን ፡ አለበት ። በተጨማ ሪም ፡ አባትነቱ ፡ እንዲተላለፍለት ፡ የሚፈልገው ፡ ሰው ፡ ሕፃኑን ፡ ልጄ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መቀበል ፡ አለበት ።

---

54. ጂ ፡ ክሽችኖቢች ፡ "የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍ. ፯፻፶፰—፯፷፩ ፤ ተጨማሪ ፡ ጭብጦች" ፤ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡ ፪ኛ ፡ ቦልዩም ፡ (፲፱፻፶፯) ፡ ገጽ ፡ ፻፹፭—፻፹፮ ፡ አስተያይ ።
55. ቍ ፡ ፯፻፷፰(፩) ፡ ከ፯፻፲፲ ፡ ጋር ።
56. ጂ ፡ ክሽችኖቢች ፡ "ሕግና ፡ ባህል ፡ (ልማድ) ፡ በኢትዮጵያ ፡" እላይ ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ ፲፮ ፡ የተጸፈው ፤ በክፍል ፡ ሕጋዊ ፡ የሆኑ ፡ መንግዶች ፡ ስለቤተ ፡ ዘመድ ፡ ሕግ ፡ የሚለው ፡ አርእስት ።
57. ቍ. ፯፻፵፪ ፡ አስተያይ ።
58. ቍ. ፯፻፹፭—፯፻፹፯ ፡ እና ፡ ፯፻፹፰ ፡ ተመልከት ።

፪ ፣ አባትነትን ፣ የሚያስተላልፈው ፣ ውል ፣ በጽሑፍ ፣ ሆኖ ፣ አራት ፣ ምስክ ሮች ፣ እንዲፈርሙበት ፣ በተጨማሪም ፣ ጉዳዩ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ቀርቦ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ እናቲቱ ፣ የምትለውን ፣ ከሰማ ፣ በኋላ ፣ አባትነት ፣ መተላለፉን ፣ በመቀበል ፣ ፈቃድ ፣ መስጠት ፣ አለበት ።

አባትነት ፣ ከተላለፈ ፣ በኋላ ፣ መሻር ፣ አይቻልም ። አባትነትን ፣ ማስወገድ ፣ የሚቻለው ፣ ልጅን ፣ አቅፎ ፣ አባትነትን ፣ በማወቅ ፣ ካረጋገጡ ፣ በኋላ ፣ መልሶ ፣ ለመሠረዝ ፣ በሚቻልበት ፣ በተፈቀዱት ፣ ሁኔታዎች ፣ ብቻ ፣ ነው ። በተፈቀዱ ፣ ሁኔታዎች ፣ ብቻ ፣ አባትነትን ፣ ማስወገድ ፣ እንዲቻል ፣ የተደረገበትን ፣ ምክንያት ፣ «አባትነትን ፣ ስለማወቅ ፣» በሚለው ፣ ሥር ፣ ተዘርዝሯል[59] ። (ያን ፣ ይመለከቷል ፣)

፭ / <u>በአባትነት ፣ ምክንያት ፣ ስለሚነሣ ፣ ክርክር</u> ።[60]

አንዲት ፣ እናት ፣ ልጅ ፣ በወለደችበት ፣ ጊዜ ፣ ከባሏ ፣ ጋርና ፣ ከጋብቻዋም ፣ ውጭ ፣ ከሌላ ፣ ሰው ፣ ጋር ፣ የግብረ ፣ ሥጋ ፣ ግንኙነት ፣ ይኖራት ፣ ይሆናል ። ወ ይም ፣ አንዲት ፣ ሴት ፣ ካንድ ፣ ወንድ ፣ ጋር ፣ በጋብቻ ፣ ተሳሥራ ፣ በነበረችበት ፣ ወቅት ፣ ልጅ ፣ ትፀንስና ፣ እሱን ፣ ፈታ ፣ ሌላ ፣ አግብታ ፣ ስትኖር ፣ ልጅ ፣ ይወለድ ፣ ይሆናል ።[61] በእንዲህ ፣ ዐይነቱ ፣ ጊዜ ፣ የሚነሣውን ፣ ለልጁ ፣ የሁለት ፣ አባት ፣ መኖ ር ፣ ችግር ፣ የኢትዮጵያው ፣ ሕግ ፣ አውጭ ፣ ሁለቱ ፣ የተባሉት ፣ ሰዎች ፣ <u>በስምም ነት</u> ፣ ከሁለቱ ፣ የትኛው ፣ አባት ፣ እንደሆነ ፣ እንዲወስኑ ፣ ይፈቅድላቸዋል ። ይህ ፣ ሲደረግ ፣ ፬ ፣ ምስክሮች ፣ እንዲኖሩ ፣ ያሻል ፣ በተጨማሪም ፣ ጉዳዩ ፣ ፍርድ ፣ ቤት ፣ ቀርቦ ፣ ፍርድ ፣ ቤቱ ፣ እናቲቱን ፣ ካዳመጠ ፣ በኋላ ፣ ፈቃድ ፣ እንዲሰጥ ፣ ያሻል ። ከላይ ፣ የተባለው ፣ የአባትነት ፣ ችግር ፣ እንዲህ ፣ በስምምነት ፣ ከተወሰነ ፣ በኋላ ፣ ስምምነቱን ፣ መሻር ፣ አይቻልም ። ስምምነቱን ፣ ለማስወገድ ፣ መሞከር ፣ አባት ነት ፣ በስምምነት ፣ ከተላለፈ ፣ በኋላ ፣ ለማስወገድ ፣ እንደመሞከርና ፣ አባትነት ፣ ልጅን ፣ በማወቅ ፣ ከተረጋገጠ ፣ በኋላ ፣ ለማስወገድ ፣ እንደመሞከር ፣ ሁሉ ፣ በጣም ፣ አስቸጋሪ ፣ ነው ። (ከላይ ፣ የተጻፈውን ፣ ይመለከቷል ፣) ሁለቱ ፣ የተባሉት ፣ ሰዎች ፣ የልጁ ፣ አባት ፣ ማን ፣ እንደሆነ ፣ በስምምነት ፣ አልወሰኑ ፣ እንደሆነ ፣ ሕግ ፣ አውጭው ፣ ራሱ ፣ የባልየውን ፣ ዐይነት ፣ ወይም ፣ ልጁ ፣ የተወለደበትን ፣ ቀን ፣ በመመልከት ፣ እነዚህን ፣ ተቀዳሚ ፣ አድርጎ ፣ በመመርኰዝ ፣ የልጁን ፣ አባት ፣ ይወስናል ።

ሐ) <u>ስለ ፣ ልጅነት ፣ ማስረጃ ።</u>

<u>መምሪያ</u> ፤

አባትነት ፣ መታወቁን ፣ የሚያስረዱ ፣ ዘዴዎች ፣ ለብቻቸው ፣ በአንድ ፣ የፍ ትሐብሔር ፣ ሕግ ፣ ክፍል ፣ ውስጥ ፣ ተዘርዝረዋል ። ከዚህም ፣ የተነሣ ፣ ከአባት ፣ ማሳወቂያ ፣ ዘዴዎች ፣ መለያየታቸውን ፣ ያሳያል ። እናትነት ፣ በመወለድ ፣ ብቻ ፣ ሲታወቅ ፤ አባትነትን ፣ (አለማስፀነስ ፣ ካልተረጋገጠ) ፣ ከላይ ፣ በተዘረዘሩት ፣ ዘዴ ዎች ፣ ማረጋገጥ ፣ ይቻላል ። ሆኖም ፣ አባትነትን ፣ ለማሳወቅ ፣ መወለድን ፣ ብቻ ፣

---

59. ቍ. ፯፻፷፰ ፤ ቍ፣ ፯፻፶፯ን ፣ አስተያይ ።
60. ቍ. ፯፻፷፮—፷፱ ፣ እና ፣ ቍ፣ ፯፻፷፰ ፣ ተመልከት ።
61. (፩) የቍጥር ፣ ፯፻፵፬ ፣ <u>እና</u> ፣ ቍጥር ፣ ፯፻፵፭(፩) ፣ ወይንም ፣ (፪) ፣ በቍጥር ፣ ፯፻፵፩ ፣ ወይንም ፣ ፯፻፵፭(፩) ውስጥ ፣ የ"ተወለደ" ፣ እና ፣ የ"ተፀነሰ" ፣ ማመዛዘኛ ፣ መካከል ።

ሳይሆን ፡ በተወለዱበት ፡ ጊዜ ፡ በናትና ፡ ባባት ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ የጋብቻም ፡ ሆነ ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የነበረ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ወይም ፡ አባት ፡ የተባለው ፡ «ልጄ ፡» ብሎ ፡ አባትነቱን ፡ ማወቁን ፡ ወይም ፡ አባትነት ፡ በስምምነት ፡ መተላለፉን ፡ ማረጋገጥ ፡ ያስፈልጋል ። አንድ ፡ ወራሽ ፡ ልጅ ፡ [62] ዘመዶቹ ፡ በሞቱበት ፡ ጊዜ ፡ አባቱንም ፡ ሆነ ፡ እናቱን ፡ ለማሳወቅ ፡ የሚያስችል ፡ ምንም ፡ ቀጥተኛ ፡ ማስረጃ ፡ በጁ ፡ አይኖረው ፡ ይሆናል ። ግን ፡ የመወለድ ፡ ምስክር ፡ ወረቀት ፡ ወይም ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ [63] እንዳለው ፡ የሚያሳይ ፡ ማስረጃ ፡ ካለው ፡ በሕግ ፡ ፊት ፡ ትክክለኛው ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ (ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ያለ ፡ ኑዛዜ ፡ እንደሚወርስ ፡ ልጅ) ፡ ይቆጠራል ። እነዚህ ፡ የማስረጃ ፡ ዐይነቶች ፡ የማያከራክሩ ፡ ናቸው ። ምክንያቱም ፡ ለየብቻቸው ፡ ተወስደው ፡ ዋጋ ፡ ያላቸው ፡ የሚሆኑት ፡ ተገቢ ፡ በሆነ ፡ ዘዴ ፡ የሚቃወማቸው ፡ [64] የታጣ ፡ እንደሆነ ፡ ነው ። ባንድነት ፡ የተወሰዱ ፡ እንደሆነ ፡ ግን ፡ በጉዳዩ ፡ ፍጹም ፡ ክርክር ፡ እንዳይነሳ ፡ ያደርጋሉ ። [65] ከዚህ ፡ ቀጥለን ፡ አከራካሪና ፡ የማያከራክሩ ፡ የአባትነትን ፡ መታወቅ ፡ የሚያስረዱትን ፡ ዘዴዎች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ እንመረምራለን ።

## ፩ / የማያከራክር ፡ የልጅነት ፡ ማስረጃ ፤

፩ / በፍትሐ ፡ ብሔሩ ፡ ሕግ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ ሕጎች ፡ [66] መሠረት ፤ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ድረስ ፤ መወለድ ፤ በመወለድ ፡ ጽሑፍ ፡ ሳይሆን ፤ ከምርመራ ፡ በኋላ ፡ በሚገኝ ፡ በታወቀ ፡ ሰነድ ፡ መረጋገጥ ፡ አለበት ። ግን ፡ አንቀጽ ፡ ፪፻፯ ፡ የሚጠቅሳቸው ፡ የታወቁ ፡ ሰነዶችን ፡ የሚያዘጋጁ ፡ የክብር ፡ መዝገብ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሹማምንት ፤ ወይም ፡ በሕግ ፡ ውል ፡ እንዲያፈራርሙ ፡ የተፈቀደላቸው ፡ ሰዎች ፡ የሉም ። ሕጉን ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውል ፡ እንዳችም ፡ ነገር ፡ ስለሌለ ፤ «ለዚሁ ፡ ጉዳይ ፡ በአገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሹማምንት ፡ ይመረጣሉ ፡» የተባለውም ፡ አልተፈጸመም ። [67]

፪ ፤ ከላይ ፡ ያልነውን ፡ በማስታወስ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አንድ ፡ የማያከራክር ፡ የልጅነት ፡ ማስረጃ ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ የሚያሳየው ፡ በ፬ ፡ ምስክሮች ፡ የተፈረመው ፡ ጽሑፍ ፡ ነው [68] ። አንድ ፡ ልጅ ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ አለው ፡ የሚባለው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ወይም ፡ ዘመዶቻቸው ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ የዚያ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የዚያች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ የሚገ

62. በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ስለመወለድ ፡ የሚነሱ ፡ ችግሮች ፡ አብዛኛውን ፡ በውርስ ፡ ጊዜ ፡ ነው ። እንዳንዴም ፡ የቀለብ ፡ መስጠት ፡ ጥያቄ ፡ ሲመጣ ፡ ይነሳል ።

63. ቍ. ፯፻፷፯—፷፰ ።

64. ቍ. ፶፭ ፡ እና ፡ ፯፻፸፭(፪) ።

65. ቍ. ፯፻፸፪ ፡ እና ፡ ፯፻፸፫ ፤ ሁለቱም ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖርን ፡ (ሌላ) ፡ እና ፡ በመወለድ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ የተደገፈን ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የሚደረግ ፡ ክርክር ፡ ተቀባይ ፡ አይገኝም ።

66. ቍ. ፫ሺ፫፻፷፭ ፡ የክብር ፡ መዝገቦች ፡ ተፈጻሚ ፡ እንዳይሆኑ ፡ እንዳገዳቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ በአስተዳደር ፡ ደንቦች ፡ ድንጋጌ ፡ ፲፱፻፴፬ ፡ ክፍል ፡ ፩፻፬(መ) ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፤ ድንጋጌ ፡ ፩ ፡ ዓመት ፡ ፬ ፡ ቍጥር ፡ ፯ ፡ በኋላ ፡ የወጣው ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቶች አዋጅ ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቍ. ፩፯ ፡ አንቀጽ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ፩ ፡ ቍጥር ፡ ፯ ፡ ያስገኘው ፡ እንዳንድ ፡ በየቦታው ፡ የተበታተኑ ፡ የመወለድና ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ምዝገባዎች ፡ ብቻ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ላይ ፡ ቀዋሚና ፡ የመሸጋገሪያ ፡ አንቀጾች ፡ ኖሩም ፡ አልኖሩም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ሆኗል ። ይህ ፡ በሕግ ፡ በኩል ፡ ያሰው ፡ ዋጋ ፡ በቀላሉ ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ።

67. ቍ. ፫ሺ፫፻፷፭(፪) ።

68. ቍ. ፯፻፸—፸፩(፩) ።

ምቱት ፡ ሲሆን ፡ ነው ። ይህ ፡ እንግዲህ ፡ ዝናን ፡ ያዘለ ፡ ስለሆነ ፡ የአህጉራዊ ፡ ኤውሮፓ ፡ ሊቃውንት ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ ከሚሉት ፡ ጋር ፡ የተመሳሰለ ፡ ነው ። በልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ ላይ ፡ የስም [69] ፡ አስፈላጊነት ፡ ተትቷል ። ይህም ፡ የቤት ፡ ዘመድ ፡ ስም ፡ ባለተለመደበት ፡ አገር ፡ ዋጋ ፡ የለውም ፡ በማለት ፡ ይሆናል ። [70]

፫ ፤ እናትነት ፡ ወይም ፡ እናትነትና ፡ አባትነት ፡ በልጅ ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ መታወቁ ፡ ሲረጋገጥ ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ አይኖርም ። ነገር ፡ ግን ፡ እናቱ ፡ ያልታወቀችለት ፡ ልጅ ፡ በልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ ምክንያት ፡ የአባቱ ፡ መታወቅ ፡ ብቻ ፡ ሊያረጋግጥ ፡ ይችላልን? [71] ምንም ፡ እንኳ ፡ «አንድ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ . . . የዚያ ፡ ሰው ፡ ወይም ፡ የዚያች ፡ ሴት ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እያሉ ፡ የሚገምቱት ፡ . . . የሚሉት ፡ ቃላት ፡ አሁን ፡ የጠየቅነውን ፡ ጥያቄ ፡ በአምንታ ፡ ቢመልሱትም ፡ እንዲህ ፡ ዐይነቱ ፡ መልስ ፡ ከሕጋዊ ፡ አቋማችን ፡ ጋር ፡ ፍጹም ፡ የማይስማማ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በፊት ፡ እንዳመለከትነው ፡ አባትነትን ፡ ለማሳዋቅ ፡ የሚረዱት ፡ ዘዴዎች ፡ እናትነትን ፡ ለማሳወቅ ፡ የሚያገለግሉት ፡ እንደ ፡ ተጨማሪ ፡ ዘዴዎች ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይኸው ፡ ክርክር ፡ በጠነከረ ፡ አኳኋን ፡ ለዚህ ፡ ዐይነቱ ፡ አቋም ፡ ማስረጃም ፡ ያገለግላል ። ለምሳሌ ፡ ከመሬት ፡ ወድቆ ፡ የተገኘን ፡ ልጅ ፡ በልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ ማስረጃ ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሊያውቀው ፡ አይችልም ፤ ልጁም ፡ ልጅነቱን ፡ ሊያረጋግጥ ፡ አይችልም ።

፪ ፤ <u>አከራካሪ ፡ የልጅነት ፡ ማስረጃ ።</u>

፩ ፤ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ልጅም ፡ ሆነ ፡ ወላጅ ፡ የልጅነት ፡ ወይም ፡ የወላጅነት ፡ ሁኔታ ፡ አይኖረው ፡ ይሆናል ፤ ማለት ፡ ልጁም ፡ እንደ ፡ ልጅ ፤ ወላጁም ፡ እንደ ፡ ወላጅ ፡ አይገመት ፡ ይሆናል ። ወይም ፡ ደግሞ ፡ የሰውየውና ፡ የሴትዮዋ ፡ ዘመዶች ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ልጁን ፡ እንደ ፡ ልጅ ፡ ወላጆቹን ፡ እንደ ፡ ወላጆች ፡ በግልጽ ፡ ካለመገመታቸው ፡ የተነሣ ፡ የልጁን ፡ ልጅነት ፡ ወይም ፡ የወላጁን ፡ ወላጅነት ፡ በመቃወም [72] ፤ ፪ ፡ ምስክሮች ፡ ክስ ፡ አቅርበው ፡ ይሆናል [73] ። በእንዲህ ፡ ዐይነቱ ፡ ጊዜ ፡ የተለየ ፡ ክስ ፡ በማቅረብ ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ የልጅነቱን ፡ ወይም ፡ ወላጅ ፡ ነኝ ፡ ብሎ ፡ የወላጅነቱን ፡ መታወቅ ፡ በክርክር ፡ ማስረዳት ፡ የልጁና ፡ የወላጁ ፡ ፈንታ ፡ ነው [74] ። የሚያስገርመው ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ክስ ፡ የተወሰነው ፡ ሥርዓት ፡ የታወቁ ፡ ሰነዶችን ፡ ለማስረጃ ፡ ማቅረብ ፡ ነው ። ግን ፡ ከላይ ፡ እንዳመለከትነው ፡ የሕጉ ፡ የመሸጋገሪያ ፡ ሕጎች ፡ እነዚህን ፡ ሰነዶች ፡ በክብር ፡ መዝገብ ፡

---

69. ስለምስቱ ፡ አስፈላጊ ፡ ነገሮች ፡ ማዞ ፡ <u>እና ፡ ማዞ ፡ ሌሰን ፡ ዲ ፡ ድፐ ፡ ሲቪል</u> ፡ (ፕሬስ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ፲፱፻፶፱ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ ቲ ፡ ኢ ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፴ ፡ አስተያይ ።
70. ቍ. ፫፻፺፪—፫ ፡ ተመልከት ።
71. ለምሳሌ ፡ አባቱ ፡ ነው ፡ ከተባለው ፡ ለመውረስ ፡ ሲሆን ።
72. እንዲህ ፡ ያለ ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ ክርክር ፡ በሁኔታው ፡ ላይ ፡ ከሚደረገው ፡ ክርክር ፡ በጥንቃቄ ፡ መለየት ፡ አለበት ። በሁኔታው ፡ ላይ ፡ የሚደረገው ፡ ክርክር ፡ (ቍ. ፯፻፷፰—፸፩) ፡ ልጁ ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ እንደሌለው ፡ ሳያስረዳ ፡ ሊያገኝ ፡ የሚያስችለው ፡ መብት ፡ እንደሌለው ፡ ነው ፡ ለምሳሌ ፡ ከተባለችው ፡ እናት ፡ አለመወለዱ ፡ ሲታወቅ ።
73. ቍ. ፯፻፸(፪) ። ስለምስክሮች ፡ አላፊነት ፡ ቍ. ፪፻፺፮ ፡ ተመልከት ።
74. ተፈላጊው ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፷፯ ፡ አስገራሚ ፡ በሆነ ፡ ዓይነት ፡ ስህተት ፡ ወደ ፡ እንግሊዝኛ ፡ ተተርጉሟል ። ክስ ፡ የማቅረቡ ፡ መብት ፡ ለልጁ ፡ ብቻ ፡ አልተወሰነም ።

ሰነድ ፣ ለሚረጋገጠው ፡ በማያከራክር ፡ ማስረጃ ፡ ተጨማሪ ፡ አድርጎአቸዋል ። ይህን ፣ «የታወቀ ፡ ሰነድ [75] ፡» ሥርዓት ፡ አከራካሪ ፡ በሆነበት ፡ የማስረጃ ፡ ወቅት ፣ ማስገባት ፡ ከላይ ፣ «የማያከራክር ፡ የልጅነት ፡ ማስረጃ ፡» በሚለው ፡ ስር ፡ በገለጥ ነው ፣ ምክንያት ፡ ማስረጃው ፡ ዋጋቢስ ፣ ሆኖ ፣ እንዲቀር ፡ ያደርገዋል ።

፪ ፤ ሥርዓቱ ፡ ማንኛቸውም ፣ ዐይነት ፡ ቢሆን ፣ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የሚቀርበው ፣ ማስረጃ ፣ የልጅና ፡ የወላጅ ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩን ፡ (ይህ ፡ የልጅ ፡ — የወላጅ ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፣ በሕግ ፡ አስተሳሰብ ፡ በማስረጃ ፡ ካልተረጋገጠ ፡ በቀር ፡ የለም ፡ ወይም ፡ ትክክል ፡ አይደለም ፡) ለማረጋገጥ ፡ ሳይሆን ፤ እንዲህ ፡ ዐይነቱን ፣ ሁኔታ ፡ እንዲ ኖር ፡ መብት ፡ መኖሩን ፡ ነው ። በሆነው ፡ የማስረጃ ፡ ዘዴ ፡ አባትነትን ፡ ለማ ሳወቅ ፡ የሚረዱት ፡ ነገሮች ፣ እነዚህም ፡ ውልደትና ፣ በተጨማሪም ፡ ለምሳሌ ፡ ጋብቻ ፣ መኖሩ ፣ ወይም ፡ አባት ፡ ነኝ ፣ ባዩ ፡ አባትነቱን ፣ ማወቁን ፤ እውነት ፡ መሆ ናቸውን ፡ ማረጋገጥ ፣ ያሻል ። በውልደት ፣ ወይም ፡ በጽንሰት ፡ ጊዜ ፡ በናትና ፡ አባት ፣ ነው ፡ በተባለው ፣ ሰው ፡ መካከል ፡ ጋብቻን ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የግብረ ፣ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ እንደ ፣ ነበረ ፡ ለማሳየት ፣ ያገለግላል ። (ነገር ፣ ግን ፣ ባባትና ፡ በልጅ ፣ መካከል ፡ አያገለግልም [76] ።)

፫ ፤ የወላጅና ፡ የልጅ ፣ ሁኔታ ፡ አለኝ ፡ በማለት ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ክስ ፣ ማቅረብ ፣ ወይም ፡ አለኝታው ፣ ራሱ ፡ ማኅበራዊ ፣ ኑሮን ፡ የሚያናውጽ ፣ ነው ። የኢትዮጵያው ፣ ሕግ ፡ አውጭ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፣ የሚፈቅደው ፡ ዳኞች ፣ «በቂ ፣ ከሆነ ፡ ከባድነት ፣ ካላቸው ፡ ተግባሮች ፡ የሚመነጩ ፡ ግምቶች ፡ ወይም ፡ ማስረ ጃዎች ፡» መኖራቸውን ፡ ተመልክተው ፡ ልዩ ፡ ፈቃድ ፡ ሲሰጡ ፡ ብቻ ፡ ነው ። [77] አስፈላጊው ፡ ምልክት ፣ ለምሳሌ ፡ የልጅ ፣ ነኝ ፣ ባዩ ፡ ወላጁ ፣ ነው ፣ የሚለውን ፡ ሰው ፣ በመልክ ፡ መምሰል ፣ ሊሆን ፡ ይችላል ። በዚህም ፡ መሠረት ፣ ልጅ ፣ ነኝ ፡ ባዩ ፣ ተጨማሪ ፡ ማስረጃ ፡ አቅርቦ ፤ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፣ አለኝ ፡ በማለት ፡ ክስ ፣ እንዲያቀርብ ፣ ፈቃድ ፡ ይሰጠው ፡ ይሆናል ።

፬ ፤ ልጅ [78] ፡ በሕይወት ፣ እስካለ ፡ ድረስ ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖርን ፡ ለመ ጠየቅ ፣ ክስ ፡ ለማቅረብ ፡ ይችላል ። የልጁ ፡ ወራሾች ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ክስ ፣ ማቅረብ ፣ የሚችሉት [79] ፡ ልጁ ፣ ሀያ ፡ ዓመት ፡ ሳይሞላው ፡ የሞተ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፤ እርሱ ፣ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ በአንድ ፡ ዓመት ፣ ጊዜ ፡ ውስጥ ፣ ብቻ ፡ ነው ።

---

75. በቍ. ፻፺፫—፺፩ ፣ ውስጥ ፣ እንደተጻፈው ።

76. ቍ. ፯፻፺፱ ፣ ከቍ. ፯፻፺፩ ፡ እና ፡ ከ፯፻፺፰ ፣ ጋር ።

77. በቍጥር ፣ ፯፻፹፫ ፣ አነጋገር ፣ ውስጥ ፣ "የሚመነጩ" ፣ የሚለው ፡ "ወዲያውና ፣ በማያጠራጥር" ፣ ሁኔታ ፣ ሲገለጥ ፣ ነው ።

78. አባት ፣ ልጁን ፣ የመካሰስ ፣ ነገር ፣ በኢትዮጵያ ፣ ያልተለመደ ፣ ነው ። በቍጥር ፣ ፯፻፹፯ ፡ አነጋገር ፣ የእናትየዋ ፣ ክስ ፣ ልጁ ፣ ከእርሰዋ፣መወለዱን ፣ ስለሞት ፣ ክርክር ፣ ነው ፣ (ሕጻናት ፣ ተሰዋውጠው ፣ ይሆናል) ።

79. እንዲህ ፣ ያለ ፡ ማገጃ ፣ የሚውለው ፡ መወለድን ፣ ለማግኘት ፡ በሚደረገው ፡ አከራካሪ ፣ የመወለድ ፣ ማስረጃ ፣ ላይ ፣ ነው ። እንደዚህ ፣ ያለ ፣ ማገጃ ፡ አከራካሪ ፡ ባልሆነ ፣ የመወለድ ፡ ማስረጃ ፡ ላይ ፣ የለም ፤ ለምሳሌ ፣ "የቤተሰብን ፡ ርስት" ፣ የሚነካ ፣ ሲሆን ፣ የተወሰነ ፣ ጊዜ ፣ የሌለው ፣ ለወራሽ ነት ፣ ጥያቄ ፣ ጉዳዮች ፡ (ቍ. ፬፻፶፱ ፣ ከ፬፻፪ ፣ ጋር) ፤ የመወለድ ፣ ሁኔታ ፣ እንዳለው ፡ የሚነካ ፣ ሲያ ስገኝ ፡ ከሚችለው ፣ "መብት" ፣ ማስረጃ ፡ ልዩነት ፣ እንዳለ ፣ ከብዙ ፣ ትውልድ ፡ በፊት ፡ የታወቀ ፣ ነው ፣ ተፈላጊ ፣ የሆኑት ፣ የዘር ፡ ሐረጎች ፣ እንኳን ፣ በዘመዳሞች ፣ መሐከልም ፣ ቢሆን ፣ ይዘበረቃሉ ። ነገር ፣ ግን ፣ እንዴት ፣ እድርጐ ፣ ቍጥር ፣ ፯፻፹፩ ፣ የሚፈልገውን ፣ አራት ፣ "ምስክሮች"ማሟላት፣ ይቻላልል ፣ ምናልባት ፣ ቀራቢውን ፣ ቍጥር ፣ ፫፻፷፰(፩) በመመልከት ፣ ለዚሁ ፣ ጉዳይ ፣ በሰፈው ፣

ከላይ ፡ ባቀረብነው ፡ ክርክር ፡ መሠረትና ፤ የልጅነት ፡ ማሳወቅ ፡ ክስ ፡ የምታቀርብ ፡ ወይም ፡ የሚቀርብባት ፡ እናቲቱ ፡ ነች ፡ በሚለው ፡ የፍትሐ ፡ ብሔር ፡ ሕግ ፡ ቍጥር ፡ መሠረት ፤ አባትነትን ፡ ማሳወቅ ፡ ከእናትነት ፡ ማሳወቅ ፡ በኋላ ፡ የሚሆን ፡ ጉዳይ ፡ ነው [80] ። እንዲያውም ፡ በሚቀጥለው ፡ ቍጥር ፡ እንደተመለከተው ፡ «የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩን ፡ ለመጠየቅ ፡ ክስ ፡ የቀረበው ፡ በማናቸውም ፡ ሲሆን ፡ ክሱ ፡ የተከናወነ ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፤ የልጁ ፡ እናት ፡ ነች ፡ የተባለችውና ፤ ልጁ ፡ ያንተ ፡ ነው ፡ የተባለው ፡ ሰው ፡ በክሱ ፡ ውስጥ ፡ እንዲገቡ ፡ ማድረግ ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ፡» ይላል ። ይሀ ፡ ከሆነ ፡ እንግዲህ ፡ አከራካሪ ፡ ወይም ፡ የሚያከራክር ፡ የልጅነት ፡ ማስረጃ ፡ አቅርቦ ፤ አባትነት ፡ መረጋገጡን ፡ ማሳየት ፤ እናትነት ፡ ከተረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ የሚሆን ፡ ነው ፤ ማለት ፡ አባትነት ፡ መረጋገጡን ፡ ማስረዳት ፡ የሚቻለው ፡ እናትነት ፡ መረጋገጡን ፡ ካስረዱ ፡ በኋላ ፡ ነው ።

፭ ፤ አንድ ፡ በልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፤ ምክንያት ፡ የታወቀ ፡ አባትነትን ፡ እንዴት ፡ ለመቃወም ፡ ይቻላል? የእናትነትን [81] ፡ ወይም ፡ የአባትነትን [82] ፡ መታወቅ ፡ በመቃወም ፡ ክስ ፡ ማቅረብ ፤ ልክ ፡ አባትነት ፡ ወይም ፡ እናትነት ፡ በእርግጥ ፡ ሳይኖር ፤ ልጅነት ፡ አለ ፡ በማለት ፡ እንደሚቀርብ ፡ ክስ ፡ ሁሉ ፤ ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ አስጊ ፡ ጉዳይ ፡ ነው ። በዚሀ ፡ ምክንያት ፤ እንዲሀ ፡ ዐይነቱ ፡ ክስ ፡ ሊቀርብ ፡ የሚችለው ፤ ዳኞች ፡ እርግጠኛ ፡ የሆኑና ፡ በቂ ፡ ከባድነት ፡ ያላቸውን ፡ ተግባሮች ፡ ተመልክተው ፡ ፈቃድ ፡ ሲሰጡ ፡ ብቻ ፡ ነው [83] ። አንድን ፡ ልጅ ፡ በማስፀነስ ፡ አስወልዷል ፡ የተባለ ፡ አባት ፤ ልጁን ፡ እንዳላስፀነሰ ፡ በማስረዳት ፡ ሊክድ ፡ የሚያቀርበውን ፤ እጅግ ፡ በጣም ፡ የተወሰነውን ፡ የክስ ፡ ዐይነት ፡ «ከጋብቻ ፡ ወይም ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በነበረ ፡ የግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ አባት ፡ ነው ፡ የሚያሰኝ ፡ ግምት ፡ «በሚለው ፡ ስር ፡ አስረድተናል ፡» የእናትነትን ፡ ማወቅ ፡ ግን ፤ ልጁ ፡ ተወልዷል ፡ በተባለበት ፡ ወቅት ፤ ልጁም ፡ ሆነ ፡ ሌላ ፡ ልጅ ፡ አለመወለዱን ፤ ወይም ፡ ከሳሹ ፡ ልጅ ፤ ተከሳሽዋ ፡ እናት ፡ ከወለደችው ፡ ልጅ ፡ የተለየ ፡ መሆኑን ፡ በማስረዳት ፡ (የኋለኛው ፡ ልጅ ፡ የመጀመሪያው ፡ ልጅ ፡ ልጅነት ፡ ይገባኛል ፡ ሲል ፡ ይከራከር ፡ ይሆናል ፡) መቃወም ፡ ይችላል ።

## <u>መ) መደምደሚያ ፤</u>

በኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ውስጥ ፡ ያሉት ፡ የአባትነት ፡ ማወቂያ ፡ ድንጋጌዎች ፤ ከኢትዮጵያውያን ፡ የጥንት ፡ ሐሳቦች ፤ ከዘመናውያን ፡ የሕግ ፡ ሐሳቦችና ፡ ዘዴ

---

በመተርጐም ፡ ነው ። "— ተወላጅ ፡ የሆነው ፡ ሰው ፡ የትውልድ ፡ ሀረጉን ፡ መዝዞ ፡ ርስቱ ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይህ ፡ የይርጋ ፡ ሕግ ፡ አያግዳም ። "ስለ ፡ ቤተሰብ ፡ ርስት" ፡ የተናኘ ፡ ወርቅ ፡ አብዲን ፡ የጀቴ ፡ ወርቅ ፡ ለገሠን ፡ ጉዳይ ፡ (ከፍተኛው ፡ ፍ/ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ፲፱፻፶፯ ዓ ፡ ም) ፡ <u>የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ መጽሔት ፡</u> ፪ኛ ፡ ቦልዩም ፡ ገጽ ፡ ፭፻ ፡ ተመልከት ። ስለ ፡ "ልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር" ፡ ከላይ ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ ፭ ፡ የተጠቀሰውን ፡ የወርቅነሽ ፡ በዛብሆንና ፡ የይድነቀው ፡ ጉዳይን ፡ ተመልከት ። (በዚሀ ፡ ፍርድ ፡ ላይ ፡ የእኛ ፡ አስተያየት ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ (ሀ) የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ በየትኛውም ፡ ደረጃ ፡ ቢሆን ፡ ሕጋዊ ፡ ሁኔታ ፡ አይደለም ። ይሀ ፡ የሚያከራክር ፡ የልጅነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖሩን ፡ ማስረጃ ፡ ማቅረቢያ ፡ ዘዴ ፡ ነው ። (ለ) የማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ ደንቦች ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሰው ፡ ሊሠሩ ፡ ይችሉ ፡ ይሆናል ። ከላይ ፡ በተራ ፡ ቍጥር ፡ ፲፬ ፡ ቍጥር ፡ ፲፱፻፷፬(፪) የተመለከተውን ፡ የካርቦኒን ፡ ጽሑፍ ፡ አስተያይ ።

80. ቍ. ፯፻፹፪(፩—፪) ። ከቍ. ፯፻፵፬ ጋር ፡ ይሀም ፡ ልጁ ፡ ከተባለችው ፡ እናት ፡ በሥጋ ፡ መወለዱን ፡ ብቻ ፡ በማረጋገጥ ፡ ነው ።

81. ቍ. ፯፻፹፭—፹፮ ።

82. ቍ. ፯፻፹፯—፺፩ ።

83. ቍ. ፯፻፹፫ ፡ ፯፻፹፬ ፡ እና ፡ ፯፻፹፯ ።

ዎች ፡ የተውጣጡ ፡ ናቸው ። ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ ከተወለዱና ፡ ከሕጋዊ ፡ ጋብቻ ፡ በተወለዱ ፡ ልጆች ፡ መካከል ፡ የነበረውን ፡ ጥን ታዊ ፡ እኩልነት ፡ በመጠበቅ ፡ ፍትሐ ፡ ብሔሩ ፤ ዛሬም ፡ የአባትነት ፡ መታወቅ ፡ የሚያስከትለውን ፡ ውጤት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አባትነትን ፡ ለማሳወቅ ፡ የሚረዱትን ፡ ዘዴዎች ፡ ጭምር ፡ ለሁለቱም ፡ ልጆች ፡ አንድ ፡ እንዲሆኑ ፡ አድርጓል ። ግን ፡ አባትን ፡ ለማወቅ ፡ የሚቀርቡትን ፡ ክሶች ፡ ለመቀነስ ፡ ሲባል ፤ በጥንቱ ፡ ሕግ ፡ ገደብ ፡ ያልነበራቸውን ፤ የአባትነት ፡ ማወቂያና ፤ አባትነት ፡ መታወቁንም ፡ የሚያ ረጋግጡ ፡ ዘዴዎችን ፡ እጅግ ፡ ቀንሷል ፤ ገደብም ፡ አብጅቶላቸዋል ። ይህ ፡ ከፈረ ንሳይ ፡ ሕግ ፡ የተወረሰ ፡ ዘዴ ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ የኢትዮጵያ ፡ የአባትነት ፡ ማወቂያ ፡ ድንጋጌዎች ፡ አከፋፈል ፡ ምንጫቸው ፡ የፈረንሳዩ ፡ ሕግ ፡ ነው ።

## ጥማሪ I

የኢትዮጵያ ፡ የሕግ ፡ መጽሔት ፡ ሳይታተም ፡ ስለዘገየ ፡ ይህ ፡ ጽሑፍ ፡ በነ ሐሴ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ. ም. ፓንጋሰ ፡ ላይ ፡ ለተደረገው ፡ ለሰባተኛው ፡ ኢንተርና ሺናል ፡ ከንግሬስ ፡ ኦፍ ፡ ኮምፓራቲብ ፡ ሎው ፡ ከቀረበ ፡ ብዙ ፡ ወሮች ፡ አልፈው ታል [84] ። ከስብሰባው ፡ ውጤት ፡ መግለጫ ፡ ጽሑፍና [85] ፡ በክፍል ፡ ፪ ፡ ሐ(፪) ከተደረገው ፡ ውይይት ፡ የሚከተሉትን ፡ አስተያየቶች ፡ አሁን ፡ ለመጨመር ፡ ይቻላል ፡—

፩ ፤ በውጭ ፡ ሀገር ፡ የሚደረገው ፡ የሕግ ፡ መሻሻል ፡ ተግባር ፡ በጋብቻና ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ የተወለዱ ፡ ልጆች ፡ እኩል ፡ ሕጋዊ ፡ አቋም ፡ እንዲኖራቸው ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ በማድረግ ፡ ላይ ፡ ናቸው ። (ወይንም ፡ አሁን ፡ በቅርቡ ፡ ብቻ ፡ ያደረጉ ፡ ናቸው ፡) እንዲህ ፡ ያለ ፡ እኩልነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ያለ ፡ ልማድ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ረገድ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሆኑ ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ የተለየች ፡ ናት ።

፪ ፤ የሩማንያው [86] ፡ ብሔራዊ ፡ ዜና ፡ አቅራቢ ፡ እንደገለጸው ፡ በጋብቻና ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ መኖር ፡ የተወለዱ ፡ ልጆች ፡ እኩል ፡ ከተደረጉ ፡ ስለ ፡ ልጅነት ፡ ማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ ደንብ ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ እንዲሁ ፡ እንዲተው ፡ ሳያደርግ ፡ አይቀርም ። የውጭ ፡ ሀገር ፡ ሕግ ፡ አሻሻዮች ፡ አስተያየትና ፡ አዝማሚያ ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡ ይህን ፡ የሚከተል ፡ ይመስላል ። ኢትዮጵያ ፡ በጋብቻና ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የሚወለዱትን ፡ ልጆች ፡ እኩል ፡ ብታደርግም ፡ አቋማቸውን ፡ ለማስረዳት ፡ የማስረጃ ፡ አቀራረብን ፡ ነገር ፡ ወሰን ፡ አድርጋበታለች ። ስለዚህም ፡ ኢትዮጵያ ፡ ከሌሎቹ ፡ ትይዩ ፡ ሀገሮች ፡ አስገራሚ ፡ ልዩነት ፡ አምጥታለች ። ወሰን ፡ እንዲደረግበትም ፡ ያደረገው ፡ ለውርስ ፡ ሲባል ፡ የሚነሱ ፡ ያአግባብ ፡ የበዙ ፤ የጠነ ጠኑና ፡ ደካማ ፡ ጥያቄዎች ፡ ናቸው ። በሶሻሊስት ፡ ሀገሮች ፡ የሚወረስ ፡ የግል ፡

84. የስብሰባው ፡ ጠቅላላ ፡ ሪፖርት ፡ በሳንትር ፡ ኢንተርዩኒበርስቴር ፡ ደ ፡ ድሮ ፡ ኮምፓር ፡ በሩሴል ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በሚወጣው ፡ ሪፖር ፡ ገኔራል ፡ ኦ ፡ ፯ኛው ፡ ኮንግሬስ ፡ ኢንተርናሲዮናል ፡ ዲ ፡ ድሮ ፡ ኮምፓሬ ፡ ታትሞ ፡ ይወጣል ። እንዲሁ ፡ ያሉትን ፡ ሪፖርቶች ፡ የሚመለከቷቸው ፡ አገሮች ፡ አት መው ፡ ያወጣቸዋል ።

85. የክሉጂ ፡ ዩኒበርሲቲ ፡ ፕሮፌሰር ፡ ኦሬሊያን ፡ ጀናስኩ ።

86. የሩማንያን ፡ ኢንስቲትዩት ፡ ኦፍ ፡ ጁሪዲካል ፡ ሪሰርች ፡ ፕሮፌሰር ፡ ጀን ፡ ሩካሬኑ ።

ንብረት ፡ ብዙውን ፡ ጊዜ ፡ በሰሌለ ፡ ወሰን ፡ የሌለው ፡ የልጅነት ፡ ማስረጃ ፡ አቀራ ረብ ፡ ይታያል ።

፫ ፤ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የአባትነት ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ በዝርዝር ፡ ለተወ ሰኑ ፡ ሁኔታዎች ፡ ብቻ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ ከሌሎች ፡ ወይም ፡ ከብዙዎቹ ፡ ስብሰባው ፡ ላይ ፡ ከቀረቡት ፡ ብሔራዊ ፡ ዜናዎች ፡ ውስጥ ፡ ያልተገኙና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕግ ፡ ቅንጅት ፡ ዓይነተኛ ፡ የሆኑትን ፡ ምልክቶች ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ተዘርዝረዋል ።

(ሀ) ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ከእናትየዋ ፡ ጋር ፡ የሚኖ ረው ፡ ሰው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ተቃራኒ ፡ ማስረጃ ፡ ሊቀርብበት ፡ የማ ይቻል ፡ ወላጅ ፡ አባት ፡ ነው ፡ የሚያሰኝ ፡ ግምት ፡ የሚሰጠው ፡ የኢትዮ ጵያ ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ለዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ባል ፡ ሆኖ ፡ ይቆጠራል ።

(ለ) በኢትዮጵያ ፡ እናትነት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ አባትነትም ፡ ያላንዳች ፡ ክር ክር ፡ የባልና ፡ የሚስትነት ፡ ሁኔታ ፡ በመኖሩ ፡ ብቻ ፡ ለማረጋገጥ ፡ ይቻ ላል ። (ሌሎች ፡ የተበረዘሩት ፡ የማስረጃ ፡ አቀራረብ ፡ ሁኔታዎች ፡ እን ዳሉ ፡ ማሳየት ፡ ሳያስፈልግ ።) በዚህ ፡ ረገድ ፡ ግልጽ ፡ ምስያ ፡ የሚገ ኘው ፡ መወሰድን ፡ የባልና ፡ የሚስትነት ፡ ሁኔታ ፡ በመኖሩ ፡ ማረጋገጥ ፡ (ቍ. ፯፻፷ ፡ (፩—፪)) ፡ እና ፡ ግዙፍነት ፡ ያለውን ፡ ተንቀሳቃሽ ፡ ንብ ረት ፡ በመያዝ ፡ ባለሀብትነትን ፡ ማረጋገጥ ፡ መካከል ፡ ነው ። (ቍ.፯፻፷፫ ከ፯፻፷፬ ፡ ጋር) ።

(ሐ) አባትነትን ፡ አውቆ ፡ መቀበል ፡ በእናቲቱ ፡ የሚደረግባቸው ፡ ብዙ ፡ አገሮች ፤ እናቲቱ ፡ ሞታ ፡ ወይም ፡ አእምሮዋ ፡ ተናውጾ ፡ እንደሆነ ፡ ዋጋ ፡ ያለው ፡ ማወቅ ፡ ሊሆን ፡ የሚችል ፡ አይመስልም ። በኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ የሚቆጠር ፡ የእናትየዋ ፡ ዘመድ ፡ ወይንም ፡ የልጁ ፡ አሳዳሪ ፡ በዚህን ፡ ጊዜ ፡ ማወቁ ፡ ተቀባይነት ፡ ሊያገኝ ፡ ይችል ፡ ይሆ ናል ።

(መ) በተንኰል ፡ የሆነ ፡ የአባትነት [87] ፡ ማወቅ ፡ ምናልባት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ አዋቂው ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ አባትነት [88] ፡ ሊኖረው ፡ በፍጹም ፡ የማይቻለው ፡ መሆኑን ፡ ካላረጋገጠ ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ለማድረግ ፡ የማ ይቻል ፡ ነው ።

(ረ) በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ባንዳንድ ፡ በተገለጹ ፡ ሁኔታዎች [89] ፡ ጊዜ ፡ ሕጋዊ ፡ የሆነው ፡ አባት ፡ አባትነት ፡ ለሌላ ፡ ልጁን ፡ ለሚቀበለው ፡ ሰው ፡ በውል ፡ ሊያስተላልፍ ፡ ይችላል ። ይህ ፡ ከውጭ ፡ ሀገሮች ፡ የሕግ ፡ ቅንጅት ፡ ጐልቶ ፡ የሚታይ ፡ ልዩነት ፡ ሊኖር ፡ የቻለው ፡ የውጭ አገር ፡ የሕግ ፡ ቅንጅቶች ፡ አጥብቀው ፡ የሚመለከቱት ፡ በሥጋ ፡ መወለ

---

87. አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ በ"አክብሮት" ፡ (በመደለል) ፡ ወይንም ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ የሚደረግ ።

88. ከቍጥር ፡ ፯፻፺፪(፪) ፡ የወጣ ፡ ተመጣጣኝ ፡ ክርክር ። ነገር ፡ ግን ፡ ልጁ ፡ ሌላ ፡ ሕጋዊ ፡ አባት ፡ ያለው ፡ ከሆነ ፡ (ቍ. ፯፻፺፯) ፡ የማወቁ ፡ ነገር ፡ ከመጀመሪያው ፡ ዋጋ ፡ የሌለው ፡ ነው ።

89. ቍ. ፯፻፹፰ ።

ድን ፡ ወይንም ፡ የሰው ፡ አካል ፡ የሚሸጥ ፡ የሚለወጥ ፡ አይደለም ፡ የሚ ለውን ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ በመከተል ፡ ነው ። ደግሞ ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ እንደተገለጸው ፡ የሁለት ፡ ሕጋዊ ፡ አባትነት ፡ መኖር ፡ ችግር ፡ ሁለት ፡ አባት ፡ ናቸው ፡ ተብለው ፡ በተገመቱት ፡ መካ ከል ፡ በውል ፡ ስምምነት ፡ ሊፈጸም ፡ ይችል ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ ከላይ ፡ የተነገረው ፡ ውል ፡ ሕጋዊ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለገንዘብ ፡ ጥቅምም ፡ ሲባል ፡ ሊደረግ ፡ የሚቻል ፡ ይመስላል ።

፬ ፤ ዘወትር ፡ «የእኩልነት ፡ አቋም ፡» እየተባለ ፡ ከሚጠራው ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ ሌላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የመወለድ ፡ ሕግ ፡ <u>መሠረታዊ ፡ አዝማሚያ</u> ፡ እንዲህ ፡ ተብሎ ፡ በአጭሩ ፡ ሊጻፍ ፡ ይቻላል ፡—

(ሀ) በመሠረቱ ፡ ነፃ ፡ የሚያከራክሩ ፡ እና ፡ በልኩም ፡ ነፃ ፡ አከራካሪ [90] ፤ በእናት ፡ በኩል ፡ ልጅነት ፡ የመወለድ ፡ ማስረጃ ።

(ለ) በመሠረቱ ፡ ነፃ ፡ የማያከራክር ፡ የአባትነት ፡ ማስረጃ ፡ ለምሳሌ ፡ የልጅ ነት ፡ ሁኔታ ፡ መኖር ፡ በኩል ።

(ሐ) (፩) <u>በአከራካሪ</u> ፤ (፪) <u>የአባትነት</u> ፡ ዝርያ ፡ (፫) <u>እንደ ፡</u> ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ የተወለደው ፡ በማንም ፡ ያልታወቁ ፡ ወይም ፡ «ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግ ብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡» ለተወለዱ ፡ የሚደረገው ፡ ወላጅ ፡ አባት ፡ ነው ፡ ስለሚያሰኘው ፡ ግምት ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በተወለዱ፡ልጆች፡ላይ ፡ የተደረገ ፡ ፍጹም ፡ ወሰን ፡ ከሦስቱ ፡ በጥቃቅን ፡ ከተጻፉት ፡ ቅጥያዎች ፡ የተነሳ ፡ የተደረገው ፡ ወሰን ፡ ቍ. ፯፻፷፩ ፡ ቃል ፡ በቃል ፡ አንብቦ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ከሚባለው ፡ ውጤት ፡ ያነሰ ፡ ነው ።

(መ) በፖሊሲ ፡ ረገድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ የመወለድ ፡ ሕግ ፡ ግልጽ ፡ ሳይሆን ፡ አንደኛው ፡ <u>ዓላማው ፡</u> የውርስ ፡ (ወይም ፡ የለብ ፡) ክርክርን ፡ ለመቀነ ስና ፡ በጋብቻም ፡ ሆነ ፡ ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ ያለውን ፡ የቤተሰብን ፡ ሰላም ፡ ለመጠበቅ ፡ ነው ። [91] ይህ ፡ ዓላማ ፤ (፩) ራሱን ፡ አሳልፎ ፡ ሳይሰጥ ፤ አንዳንዴ ፡ ከማይገጣጠመው ፡ የሰው ፡ ፍጥረት ፡ ሁኔታና ፡ የልጁን ፡ ጥቅም ፡ አጠባበቅ ፡ ዓላማ ፡ ጋር ፡ በጥንቃቄ ፡ የተመዛዘነ ፡ ነው ፤ [92] (፪) አንዳንዴም ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ ላይ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ አካሉን ፡ አሳልፎ ፡ አይሰጥም ፡ የሚለውን ፡ መሠረታዊ ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ ገኖ ፡ ይታያል ። [93]

---

90. "በልክ" ፡ የሚለው ፡ ቅጥያ ፡ የሚያመለክተው ፡ አስቀድሞ ፡ ክሱን ፡ ለመጀመር ፡ የፍርድ ፡ ቤት ፡ ፈቃድ ፡ ማግኘትን ፡ ነው ። ቍ. ፯፻፸፫—፸፬ ። ከዚህ ፡ ወዲያ ፡ በእርግጥ ፡ ልጁ ፡ መወለዱን ፡ ለማ ስረዳት ፡ በማንኛውም ፡ ዓይነት ፡ ይቻላል ። (ይህ ፡ በግልጽ ፡ የአባትነትን ፡ ነገር ፡ <u>አይደለም) ።</u>

91. አባትነትን ፡ ስለማስረዳት ፡ የተደረጉ ፡ ማገጃዎችና ፡ ቢረጋገጥም ፡ የሚወጣውንም ፡ ክርክር ፡ (በመካድ ፡ ጊዜ) ፡ ቢሆን ፡ በሁሉቱም ፡ አይደገፍም ።

92. ለምሳሌ ፡ በቍ. ፯፻፶፩—፶፪ ፡ ውስጥ ፡ ስለመቀበል ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ነገሮች ፡ ወይም ፡ በቍ. ፯፻፷፫ ፡ እና ፡ ፯፻፷፯ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም፡ ቢፈቅድ፡ የሚያስገኝ፡ ነው። ሁለቱም፡ አላማዎች፡ "ከጋብቻ ፡ ውጭ ፡ በግብረ ፡ ሥጋ ፡ ግንኙነት ፡ ስለ ፡ መኖር" ፡ በሚደረገው ፡ አባት ፡ ነው ፡ በሚያሰኘው ፡ ግምት ፡ ጊዜ ፡ በአንድ ፡ ላይ ፡ ይሆናሉ ።

93. ቍ. ፯፻፷፱ ፡ እና ፡ ፯፻፷፰ ፡ ተመልከት ።